ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ማክሰኞ

82ኛ ዓመት ቁጥር 171 የካቲት 21 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


# ዓድዋ ለዜጎች ነፃነትና ለሀገራዊ አንድነት በጋራ የመቆም ተምሳሌት ነው

**ጌትነት ተስፋማርያም**




አዲስ አበባ፡- በአባቶች ተጋድሎ የተገኘው የዓድዋ ድል ልዩነቶችን ወደጎን በመተው ለዜጎች ነፃነትና ለሀገራዊ አንድነት በጋራ የመቆም ተምሳሌትነትን በተግባር ያሳየ ድል ነው ሲሉ የታሪክ ተመራማሪውና መምህሩ ዶክተር አየለ በከሬ ተናገሩ።

ዶክተር አየለ በከሬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ምልክት የሆነው ዓድዋ ከተለያዩ አካባቢዎች በአንድነት መንፈስ በተሰባሰበው ኢትዮጵያውያን ያስገኙት ድል በመሆኑ ተምሳሌትነቱ ከፍ ያለ ነው።

የዓድዋ ድል ኢትዮጵያዊነትና ሕብረ ብሔራዊነትን ከማጠናከር አኳያ ያለው አንድምታ ከፍ ያለ ነው ያሉት የታሪክ ምሁሩ፤ ማንነታቸው ኢትዮጵያዊ የሆኑና የተለያየ ቋንቋ፣ ባህል፣ አስተሳሰብና አኗኗር ያላቸው ሰዎች በወቅቱ ጣሊያን ሊወረን መምጣቱን በመገንዘብ የአገራቸውን ክብር ለማስጠበቅ ልዩነት ሳይገድባቸው በዱር በገደሉ በአንድነት ተዋድቀዋል ሲሉ አስረድተዋል።

አንተ ከንባታ ነህ፣ አንተ ኦሮሞ ነህ፣ አንተ አማራ ነህ፤ አንተ ከትግሬ ነህ ወዘተ ሳይባባሉ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በተደራጀ መንገድ በሀገር ፍቅር ስሜት ተነሳስተው ያስገኙት ድል በመሆኑ ሁሌም ሊታወስ ይገባል ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

እንደ ዶክተር አየለ ገለጻ፤ የአገራቸው ህልውና አስጊ በሆነበት ወቅት መሬታችንን አናስደፍርም በማለት የተፋለሙ አርበኞች ለዛሬው ትውልድ ስነልቦናዊ ውቅር መዳበር የሚበጅ ታሪክ በደማቅ ቀለም ጽፈዋል።

ዓድዋ ለዜጎች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








አቶ ንጉሡ ጥላሁን

# የሥራ አጥ ቁጥርን ለመቀነስ የአገናኝ ኤጀንሲዎች ሚናቸውን ማሳደግ አለባቸው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን የሥራ አጥ ቁጥር ለመቀነስ የግል አሰሪና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ሚናቸውን ማሳደግ እንዳለባቸው የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በተለያዩ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ከሚገኙ የግል አሰሪና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ጋር በዘርፉ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚረዳ ምክክር አካሂዷል።

በመድረኩ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሡ ጥላሁን እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ እየታየ ያለውን የሥራ አጥ ቁጥር ለመቀነስ የግል አሰሪና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች ሚና የጎላ መሆን አለበት።

ኤጀንሲዎቹ ወጣቱ በተለያዩ ዘርፎች ላይ ያለውን ክህሎት እንዲያሳድግ በተሻለ መንገድ ከተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር መስራትና በርካቶች የስራ ዕድል እንዲያገኙ ማገዝ አለባቸው ብለዋል።

የሥራ አጥ ቁጥርን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ባበክር ኸሊፋ

# ክልሉ በሌማት ቱሩፋት አንድ ሺህ የንብ ቀፎዎችን ለማሠራጨት እየሠራ ነው

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- በሌማት ቱሩፋት መርሃ ግብር አንድ ሺህ የንብ ቀፎዎችን ለማሰራጨት እየሠራ መሆኑን የቤኒሻንጉል ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡

ክልሉ በሌማት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የዓድዋ ሙዚየም ግንባታ 78 ነጥብ 2 በመቶ ደርሷል

## -ፕሮጀክቱ በሚቀጥለው ዓመት ጥቅምት ወር ይጠናቀቃል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የዓድዋ ድል መታሰቢያ የሆነው የዓድዋ ሙዚየም ግንባታ ፕሮጀክት አፈጻጸም 78 ነጥብ 2 በመቶ መድረሱ ተገለጸ። ፕሮጀክቱ በሚቀጥለው ዓመት ጥቅምት ወር ሙሉ ለሙሉ ይጠናቀቃል።

በአዲስ አበባ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት የኮንትራት አስተዳደር ዳይሬክተር ዳዊት ጥበቡ (ኢንጅነር) ትናንት ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት መግለጫ፤ የዓድዋን ድል ታሪካዊ ዳራ መነሻ አድርጎ እየተገነባ የሚገኘው ዓድዋ ሙዚየም ግንባታ ፕሮጀክት ፊዚካል አፈጻጸም 78 ነጥብ ሁለት በመቶ ደርሷል።

ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ የከተማ አስተዳደሩ በትላልቅ ግንባታ ፕሮጀክቶች በኩል የተለያዩ ፕሮጀክቶችን እያስገነባ ይገኛል። ፕሮጀክቶቹ ዘርፈ ብዙ አገልግሎት

የዓድዋ ሙዚየም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ዳዊት ጥበቡ (ኢንጅነር)






ገጽ 3

**“በትግራይ ሽግግር መንግስት የአንድ ፓርቲ የበላይነት እንዳይፈጠርና እንደገና ወደ ችግር እንዳይገባ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል”**

- አቶ አታኽልቲ ኃይለስላሴ
የቀድሞ የመቀሌ ከተማ ከንቲባ

ዜና

# ለ30 ሺህ ዜጎች ነጻ የዓይን ህክምና አገልግሎት ሊሰጥ ነው

ውብሸት ሰንደቁ

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በወራቤ፣ በጅማ እና በአዲስ አበባ ለሚገኙ 30 ሺህ ዜጎች ከፓኪስታን የሚመጡ ዜጎች ነጻ የዓይን ሕክምና ሊሰጡ መሆኑ ተገለጸ።

የአለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና ያሲን ፋውንዴሽን በትናንትናው ዕለት በሰጡት የጋራ መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በወራቤ፣ በጅማ እና በአዲስ አበባ ለሚገኙ 30 ሺህ ዜጎች ነፃ የዓይን ሕክምና ከፓኪስታን በሚመጡ የዘርፉ ባለሙያዎች ይሰጣል።

የአለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ዓለምሰገድ ጫኔ በመግለጫው ላይ እንደተናገሩት፤ ኅብረተሰቡ ይህን አጋጣሚ ማግኘቱ ትልቅ ዕድል ሲሆን በአብዛኛው አቅመ ደካማ የሆኑ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥሪ አቅርበዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ይህ አገልግሎት ሲሰጥ የአሁኑ ለሦስተኛ ጊዜ መሆኑን የተናገሩት ዳይሬክተሩ፤ መርሃ ግብሩ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ተቋርጦ መቆየቱን አስታውሰዋል።

በሚሰጠው የዓይን ሕክምና አገልግሎት ምንም ዓይነት የሪፈራል ወረቀት እና ክፍያ እንደማያስፈልግ ገልጸው፤ የሕክምና ሥራው በመደበኛው የሕክምና ሥራ ያልተሸፈኑ ዘርፎችን መሸፈን የሚያስችል እንደሆነ ተናግረዋል።



የሚሰጠው የዓይን ሕክምና የማማከር አገልግሎትን ጨምሮ የመነፅር ድጋፍ እና ቀዶ ህክምና የሚያስፈልጋቸውን የሚያካትት ነው ያሉት አቶ ዓለምሰገድ፤ በሦስቱም ከተሞች በእያንዳንዳቸው 10 ሺህ ዜጎችን ለማከም ዝግጅት መደረጉን ተናግረዋል። ከነዚህም መካከል በአጠቃላይ 1200 የሚሆኑት የቀዶ ጥገና አገልግሎት የሚያገኙ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የያሲን ፋውንዴሽን መሥራች እና ዋና ሥራ አስኪያጅ ዶክተር ያሲን ረጁ በበኩላቸው፤ የዓይን ሕክምና ሊሰጥባቸው የተመረጡት ቦታዎች የጤና ሚኒስቴርን መረጃ መሰረት አድርጎ የተመረጡ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ የዓይን ሕክምናውን የሚሰጠው የሕክምና ቡድን ከዚህ ቀደም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በመዘዋወር አገልግሎት እንደሰጠ ጠቁመዋል።

በአጠቃላይ እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር ከ2000 እስከ 2019 በኢትዮጵያ በተለያዩ ክልሎች በመዘዋወር ከ684 ሺህ በላይ የዓይን ሕክምና አገልግሎት በነፃ መስጠቱን አንስተው፤ ከዚህ ውስጥ ከ70 ሺህ በላይ የሚሆኑ ዜጎች የዓይን ቀዶ ሕክምና አገልግሎት ማግኘታቸውን ተናግረዋል።

አገልግሎቱ የሚሰጠው በአዲስ አበባ በአለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ከመጋቢት ስምንት እስከ መጋቢት 12 ቀን 2015፤ በጅማ ከተማ ከመጋቢት አንድ እስከ መጋቢት አምስት እንዲሁም በወራቤ ከተማ ከየካቲት 24 እስከ 28 2015 ዓ.ም ድረስ መሆኑን መርሃ ግብሩ አመላክቷል።



ኡስታዝ አቡበክር አህመድ

# ባንኮቹ በፋይናንስ ዘርፉ ላይ የማህበረሰቡን እኩል ተሳታፊነት ለማረጋገጥ ወሳኝ ናቸው

አመስወርቅ ከበደ

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ከወለድ ነጻ ባንኮች ማህበረሰቡ በፋይናንስ ዘርፉ ላይ እኩል ተሳታፊ እንዲሆን ያላቸው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ተገለጸ።

የሂጅራ ባንክ የሸሪያ ቦርድ አማካሪና ሰብሳቢ ኡስታዝ አቡበከር አህመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከወለድ ነጻ ባንኮች ከወለድ ነጻ የሆነ አገልግሎት የሚፈልጉ የማህበረሰብ ክፍሎች በፋይናንስ ዘርፉ እኩል ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋል።

ኡስታዝ አቡበከር እንደተናገሩት፤ በአገሪቱ ላይ በርካታ ቁጥር ማህበረሰብ አለ። ይህ ማህበረሰብ ስራዎቹን ለማስፋት፣ በአገር ልማትም ሆነ ኢንዱስትሪ ውስጥ ለመሳተፍ የባንክ ስርአቱ ስለማይፈቅድለት ከፋይናንስ ስርአቱ የተገለለበት ሁኔታ ነበረ።

አሁን ላይ እነዚህ ባንኮች ወደስራ መግባታቸው እነዚህ ከባንክ ስርአቱ ውጪ የነበሩ የማህበረሰብ ክፍሎች አቅማቸውን እንዲያሳድጉ እና ለራሳቸውም ሆነ ለአገራቸው የተሻለ ስራ እንዲሰሩ ይረዳል ሲሉ አስረድተዋል።

ይህን የወለድ ስርአቱን በመፍራት ገንዘባቸውን ወደባንክ የማያመጡ እና ቤታቸው ውስጥ በባህላዊ መንገድ የሚያስቀምጡ የማህበረሰብ ክፍሎችም ገንዘባቸውን ወደባንክ ማምጣት እንዲጀምሩ ይረዳቸዋል ሲሉ አክለው ገልጸዋል።

በአገሪቱ ከወለድ ነጻ የሆነ የፋይናንስ ስርአት በመጀመሩ ወደኋላ የቀረው ማህበረሰብ ወደፊት እንዲመጣ አገሩን እና ማህበረሰቡን እንዲያሳድግ አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው። በመሆኑም አሁን ላይ የተጀመሩት ከወለድ ነጻ ባንኮችም ይሄን እያሳዩ ነው ብለዋል።

ኡስታዝ አቡበከር እንደተናገሩት፤ እነዚህ ከወለድ ነጻ የሆኑ ባንኮች የሸሪያ ህግን መሰረት አድርገው የተመሰረቱ ሲሆን፤ ካሉት ባንኮች ልዩ የሚደርጋቸው ትርፍንም ኪሳራንም መጋራታቸው ነው ሲሉ አስረድተዋል።

ከወለድ ነጻ የሆኑ ባንኮች መኖራቸው ዜጎች ባላቸው ማንነት እና በሚፈልጉት ሁኔታ እኩል የፋይናንስ ስርአቱ ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋል ሲሉ ገልጸዋል።

በመሆኑም የባንኩ ስርአት የሚከተለው የሸሪያን የንግድ ፍልስፍና ቢሆንም፤ የንግድ ስርአት ዘርፉ፣ቀለምን፣ ሃይማኖትን የሚለይ አይደለምና ከወለድ ነጻ በሆነው ስርአት መገልገል የሚፈልግ ክርስቲያንም ሆነ ሙስሊም ባለቤት ከመሆን ጀምሮ እስከ ትግበራው ድረስ እኩል ተሳታፊ ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል።

ሰብሳቢው እንደገለጹት፤ በሸሪያው ሙጋራባ፣ ሙሻራካ የተባሉ እና የተለያዩ የባንክ የአገልግሎት አሰጣጥ አይነቶች አሉ። በአገራችን አሰራሩ በደንብ ስላላደገ እስካሁን የአገልግሎት አይነት ከሁለት አልበለጠም፤ በቀጣይ አገልግሎቱን ለማስፋት ባንኮቹ መስራት አለባቸው።

ኡስታዝ አቡበከር እንደተናገሩት፤ እስካሁን ከወለድ ነጻ ባንኮች አሰራርን በተመለከተ በቂ እውቀት ያለው ባለሙያ በብሄራዊ ባንክ ውስጥ አባል አልሆነም። አገልግሎቱ የተሳለጠ እንዲሆን እራሱን የቻለ ከወለድ ነጻ ባንክ ዳይሬክቶሬት መኖር አለበት። በዚህም ብሄራዊ ባንክና የገንዘብ ሚኒስቴር መስራት አለባቸው ሲሉ ገልጸዋል።

# ሦስት ሆስፒታሎች የዲጂታል ጤና አገልግሎትን ተግባራዊ አደረጉ

## - 24 የጤና ተቋማት የዲጂታል አገልግሎቱን ይጀምራሉ

ማርቆስ በላይ

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የዲጂታል ጤና አገልግሎት በሶስት ሆስፒታሎች ተግባራዊ መደረጉን የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ አስታወቀ።

በ2015 በጀት ዓመት መጨረሻ ለተገልጋዮች የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት አራት ተጨማሪ ሆስፒታሎች እና 20 ጤና ጣቢያዎች በአጠቃላይ 24 የጤና ተቋማት የዲጂታል ጤና አገልግሎቱን እንደሚጀምሩ ተገልጿል።

የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዮሐንስ ጫላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ጥሩነሽ ቤጂንግ፣ የካቲት 12ና አበበች ጎበና ሆስፒታሎች ሙሉ በሙሉ ወደ ዲጂታል ጤና አገልግሎት ትግበራ ገብተዋል።

በተጨማሪም በዓመቱ መጨረሻም ራስ ደስታ፣ ጋንዲ መታሰቢያ፣ ዘውዲቱ እና ምኒልክ ሆስፒታሎች በ2015 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ የዲጂታል አገልግሎቱን እንዲጀምሩ ይደረጋል ብለዋል።

እንደ ዶክተር ዮሐንስ ገለጻ፤ በአራቱ ሆስፒታሎች የትግበራ ሥራው ከ50 በመቶ በላይ ተጠናቋል። በመሆኑም ከግብዓት አቅርቦት ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ችግሮች ቢኖሩም በዚህ ዓመት አስፈላጊ እቃዎችን በማሟላት ወደ ሥራ ለማስገባት እየተሰራ ነው።

የጤና የመረጃ አያያዝ ሥርዓት መዘመን አለበት ያሉት ኃላፊው፤ የዲጂታል ሥርዓቱ በመረጃ ላይ ተመስርቶ ውሳኔ ለመስጠት፣በጤና ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ጥራት ለማስጠበቅ ጥቅም ላይ ይውላል ሲሉ አስረድተዋል።

ዶክተር ዮሐንስ እንዳስታወቁት፤ ዲጂታል አሰራሩ የወረቀት ወጪን በማስቀረት እና የስራ ቅልጥፍናን በማሳደግ የተገልጋዮችን እርካታ የሚያሳድግ ነው።

ሥርዓቱ በተገልጋዩ በኩልም ይስተዋሉ የነበሩ እንግልቶችን የሚቀንስ ነው ያሉት ዶክተር ዮሐንስ፤ በተለይ ካርድ ሳይዙ ወደጤና ተቋማት የሚመጡ



ተገልጋዮችን ለማስተናገድ፣ የተለያዩ የጤና መረጃዎችን ዳግም ይዘው ለማይገኙ ሰዎችና የተመዘገበን መረጃ ከማቅረብ ባለፈ የፋይል መጥፋትን ችግር ለመከላከል ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ተናግረዋል።

ለዚህ ተግባር በየደረጃው ያሉ ባለሙያዎች ግንዛቤ እየተሰጠ እንደሆነና የሥርዓቱ አስፈላጊነት ላይ ግንዛቤ ከመስጠት ጎን ለጎን አሰራሩ ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለማስተካከል የሚያስችል ቁጥጥር በጋራ እየተከናወነ መሆኑን ኃላፊው ገልጸዋል።

በሆስፒታሎች የተጀመረውን አገልግሎት ወደ ጤና ጣቢያዎች ለማስፋት በተሰራ ሥራ በአሁኑ ጊዜ አራት ጤና ጣቢያዎች ወደ አገልግሎቱ መግባታቸውን ገልጸው፤ በአሁኑ ጊዜ ስምንት ለማድረስ እየተሰራ ነው ብለዋል። በተያዘው ዓመት በ20 ጤና ተቋማት ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ እየተሰራ መሆኑንም ኃላፊው አስረድተዋል።

ሶፍትዌር አበልጽጎ የዲጂታል ጤና አገልግሎትን በሆስፒታሎችና በጤና ጣቢያዎች ተደራሽ ለማድረግ ከ100 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ እንደሚጠይቅ የገለጹት ዶክተር ዮሀንስ፤ ወጪው ሶፍትዌሩ ተጭኖ ግልጋሎት የሚሰጥበትን ኮምፒውተሮች እንደማይጨምርም ጠቁመዋል።

በአጠቃላይ መሰረተ ልማቱን በ101 ጤና ጣቢያዎችና በሰባት ሆስፒታሎች ተግባራዊ አድርጎ ለማስፋት ብዙ ወጪ የሚጠይቅ መሆኑን ተቁመው፤ የኔትወርኩ ዝርጋታ በሁሉም አገልግሎት መስጫ ተቋማት ላይ የሚዘረጋ ይሆናል ሲሉ አብራርተዋል።

በተያዘው ዓመት መጨረሻ በተጨማሪ አራት ሆስፒታሎችና 20 በሚደርሱ ጤና ጣቢያዎች አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግ ከተማ አስተዳደሩ በጀት በጅቶ እየሰራ መሆኑን አመላክተዋል።

# ውጤታማ የሥራ ስምሪት ለመፍጠር አባል ሀገራት በጋራ መሥራት አለባቸው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ውጤታማ፣ መደበኛ የሥራ ስምሪት ለመፍጠር እና የሚያጋጥሙ መዋቅራዊ ችግሮችን ለመፍታት አባል ሀገራቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ መስራት እንደሚጠበቅባቸው የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ። በሠራተኛ ሥራ ስምሪትና የሠራተኛ ፍልሰት ላይ ትኩረት ያደረገ የኢጋድ አባል ሀገራት ሁለተኛው የሚኒስትሮች ኮንፈረንስ መካሄድ ጀምሯል።

የአባል ሀገራቱ የባለሙያዎች ስብሰባ ላይ ተገኝተው በትናንትናው ዕለት ንግግር ያደረጉት በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የአሰሪና ሠራተኛ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ አሰግድ ጌታቸው እንደገለጹት፤ በሕዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት በየዓመቱ ወደ ሥራ የሚገቡ ብዙ አዳዲስ ሠራተኞች አሉ።

ውጤታማ፣ መደበኛ የሥራ ስምሪት ለመፍጠር መዋቅራዊ ችግሮች እያጋጠሙ ነው ያሉት አቶ አሰግድ፣ ይህን ችግር በአባል ሀገራት አቅም ብቻ መፍትሔ ለመስጠት አስቸጋሪ በመሆኑ ከባድርሻ አካላት ጋር በጋራ መሥራት እንደሚጠበቅ ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ የፍልሰት አስተዳደር ደካማ መሆን ለትውልድ፣ ለመተላለፊያና ለመድረሻ ሀገሮች እና በራሳቸው በስደተኞች ላይ ትልቅ አደጋን እያስከተለ ነው። እንደዚህ አይነት ተግዳሮቶችን ለመፍታት በዓለም አቀፍ፣ በአገርና በክልላዊ ደረጃ መመካከር፣ መወያየትንና በትብብርና በውህደት መሥራትን ይጠይቃል።

ዜጎቻችን በመዳረሻ ሀገራት የሚያጋጥሟቸውን ወሳኝ የጥበቃ ስጋቶች ለመፍታት በጋራ መስራት አስፈላጊ ነው ያሉት አቶ አሰግድ፤ የዓለም የሠራተኞች ድርጅት በክልል ደረጃ ያለው አጋርነትና የልምድ ልውውጥ በወንድማማችነት መንፈስ በመሥራት የጋራ ግባችንን እንድናጠናክር ያደርጋል ብለዋል።

የኢጋድና የዓለም የሠራተኞች ድርጅት በሥራ ስምሪት ላይ ያላቸውን ስትራቴጂ፣ አካሄዶችና ጣልቃ ገብነቶች



አቶ አሰግድ ጌታቸው

በተመለከተ ስትራቴጂ እንዲቀርጹ ለመርዳት ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ መሆኑን ገልጸው፤ በተለይም ኢጋድ ለሰላምና ለደህንነት፣ ለኢኮኖሚ ልማትና ለትክክለኛ ሥራ፣ ለመደበኛ የጉልበት ፍልሰትና ለቀጠናዊ ውህደት ያለው ቁርጠኝነት የሚያስመሰግን መሆኑን አውስተዋል።

የኢጋድ ዋና ጸሃፊ ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁን በመወከል ንግግር ያደረጉት በኢጋድ የማህበራዊ ጉዳይ ዳይሬክተር ፋቲያ አልዋን እንደገለጹት፤ በኢጋድ አባል ሀገራት ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዘው ወጣቱ የማህበረሰብ ክፍል ነው። 62 በመቶ ከ25 ዓመት በታች ዕድሜ ያለው ነው። ይሁን እንጂ ከፍተኛ ድህነትና ሥራ አጥነት ሰፍኖ ይገኛል። ቀጠናው ግጭት የማይለየው በመሆኑ፣ ድርቅና የጎሳ ግጭቶች ጉዳዩን እንዳባባሱት አንስተው፤ በርካታ ወጣቶች ለሥራ ፍለጋ ወደ ሌሎች ሀገራት እንደሚሰደዱ ገልጸዋል።

አባል ሀገራቱ የሥራ ስምሪትና የሠራተኛ ፍልሰተኞች ማዕቀፍ የሌላቸው መሆን ሌላው ችግር ነው ያሉት ዳይሬክተሯ፤ ይህን ችግር ለመቅረፍ ሥራ ስምሪትና የሠራተኛ ፍልሰት ላይ ስምምነት ከመድረስ ጀምሮ በጋራ እየተሠራ መሆኑን አንስተው፤ እ.አ.ኤ በ2021 አባል ሀገራቱ ሥራ ስምሪትና የሠራተኛ ፍልሰት ስምምነት በማጽደቅ ወደ ሥራ መግባታቸውን እንደማሳያ አንስተዋል።

# "በትግራይ ሽግግር መንግስት የአንድ ፓርቲ የበላይነት እንዳይፈጠርና እንደገና ወደ ችግር እንዳይገባ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል"

- አቶ አታኽልቲ ኃይለስላሴ
የቀድሞ የመቀሌ ከተማ ከንቲባ

**ሄርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አባባ፡- አዲስ በሚመሰረተው የትግራይ ሽግግር መንግስት የአንድ ፓርቲ የበላይነት እንዳይፈጠርና እንደገና ወደ ችግር እንዳይገባ ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ የቀድሞ የመቀሌ ከተማ ከንቲባ አቶ አታኽልቲ ኃይለስላሴ ተናገሩ። በሀገራቸው ጉዳይ ይመለከተናል የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ ሲቪክ ማህበራትን እንዲሁም ዲያስፖራውን ሊያካትት እንደሚገባም ገልጸዋል።

አቶ አታኽልቲ ኃይለስላሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት መረጃ እንደተናገሩት፤ ወደ ሽግግር መንግስቱ ለመግባት ዋናው ቁልፍ ተደርጎ መወሰድ ያለበት የፕሪቶሪያው ስምምነት እንደሆነ በማስታወስ፤ በስምምነቱ መሰረት ለትግራይ ህዝብ የሚጠቅሙ እና የሚመለከታቸው ፓርቲዎች፣ ማህበራት፣ ምሁራንና ዲያስፖራው ሊሳተፉ እንደሚገባ ነው የገለፁት።

ሽግግሩን በተመለከተ የፌዴራል መንግስት እና ሕወሓት በመነጋገር አስፈላጊ የፀጥታ ስርዓት ሊያመቻቹ እንደሚገባ የጠቀሱት አቶ አታኽልቲ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሁም ዲያስፖራው እንዲሳተፍ በማድረግ ሁሉም በራሱ ተነሳሽነት ሊሰራ እንደሚገባ፤ ዳግም የአንድ ፓርቲ የበላይነት እንዳይፈጠርና እንደገና ወደ ችግር እንዳንገባ፤ በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ሁሉም የትግራይ ተወላጅ ሊያስበው የሚገባ፤ይህ ሁሉ ችግር ለምን እንዳጋጠመን፣ምን ብናደርግ ወደ ተሻለ አቅጣጫ ልናመራ እንደሚገባ ምክንያቶቹን በማስቀመጥ ወደ መፍትሄ ሊገባ እንደሚገባ አቶ አታኽልቲ ጠቁመው፤ በተለይ ምሁራን፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የዲያስፖራ አባላት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለውጥ ለማምጣት አቅም



ስለሚኖራቸው ሊሳተፉ ይገባል ነው ያሉት።

ለቀጣይ መደበኛ መንግስት ስለሚያስፈልግ፤ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ የሰላም ስጋት እንዲወገድ እና የተስተካከለ ሁኔታ እንዲፈጠር ከወዲሁ አቅም በማካበት፤ አካሄድ ማሳመር እንደሚገባ እና በተለይ ወጣቱ ካለፈው ተምሮ የራሱ መልካም ታሪክ እንዲሁም የተሻለች ሀገር ለመገንባት ከወንድሞቹ ጋር ተስማምቶ በአንድነት ሊኖር እንደሚገባ አቶ አታኽልቲ ተናግረዋል።

# በክልሉ ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት የተፋሰስ ልማት ሥራ እየተከናወነ ነው

## -ለአረንጓዴ አሻራ ከአንድ ቢሊዮን በላይ ችግኞች ለማፍላት ታቅዷል

**ዳግማዊት ግርማ**

ሀዋሳ ፡- በደቡብ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል አራት ቢሊዮን ብር የሚገመት ህብረተሰብ አቀፍ የተፋሰስ ልማት ስራ እየተከናወነ መሆኑ ተገለጸ። በንቅናቄው 293 ሺህ ሄክታር መሬት የተፋሰስ ልማት ለማካሄድ መታቀዱም ተመልክቷል።

የክልሉ ግብርና ቢሮ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ኃላፊ አቶ አንደኛ ሽናሌ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤በክልሉ በየቀኑ ከሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን በላይ ህዝብ የሚሳተፍበት የተፋሰስ ልማት ሥራ እየተከወነ ነው። ይህ የተፋሰስ ልማት ስራም በገንዘብ ሲተመን ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ ይሆናል።

ሰላሳ አምስት ቀናት የሚቆየውና እስካሁን አስራ አምስት ቀናትን ባስቆጠረው የተፋሰስ ልማት ስራ አበረታች ውጤቶች መመዝገባቸውን አቶ አንደኛው ገልጸው፤ በክልሉ በአጠቃላይ በዘንድሮው ዓመት 293 ሺህ ሄክታር ተፋሰስ ለማልማት መታቀዱን ተናግረዋል።

አቶ አንደኛው በዘንድሮው ህብረተሰብ አቀፍ የተፋሰስ ልማት እንቅስቃሴዎች አዲስ ስፍራዎች ላይ ሳይሆን ነባሩን በጥራት የመስራት ላይ ትኩረት መደረጉን አመልክተዋል።

በተለይ የአካባቢ መራቆትንና የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን ለመከላከል፣ የአፈርና ውሃ እቀባ ስራን ለማጠናከር እንዲቻል የእርከን ስራን በልዩ ትኩረት ለመምራት እቅድ መነደፉን ተናግረዋል።

የተፋሰስ ልማት እንቅስቃሴው በክልሉ በሚገኙ ሁሉም ዞኖችና ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ ሶስት ሺህ 100 ተፋሰሶች ላይ ተግባራዊ መሆኑንም ገልጸዋል።

በክልሉ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ስራዎችን በጥራትና በተያዘው የጊዜ ሰሌዳ ለማጠናቀቅ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመው፤ በዚህም አራት ቢሊዮን ብር የሚያወጣ ስራ በህብረተሰቡ ተሳትፎ እንደሚሰራ አቶ አንደኛ አብራርተዋል።

አረንጓዴ አሻራን በሚመለከትም በክልሉ ከሚያዝያ እስከ ነሀሴ ባሉት ወራት አንድ ቢሊዮን ችግኝ የመትከል እቅድ ሲኖር በተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ ላይ ብቻም ከ300 ሚሊዮን በላይ ችግኞች መዘጋጀታቸውን አቶ አንደኛው ተናግረዋል።

የተፋሰስ ልማት እንቅስቃሴው በክልሉ በሚገኙ ሁሉም ዞንና ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ ሶስት ሺህ 100 ተፋሰሶች ላይ ተግባራዊ እንደሚሆንም አቶ አንደኛው ገልጸዋል።

# የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የአንድ ወቅት ሳይሆን ዘላቂ ልምዳችን ሲሆን ይገባል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ሀገር ተረካቢ ትውልድን በማፍራት የሀገር ግንባታ ስራዎችን ለማሳደግ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የአንድ ወቅት ተግባር ሳይሆን ዘላቂ ልምዳችን ሊሆን ይገባል ሲሉ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ወርክ ትምህርት ክፍል መምህር ጋሻነው ወርቁ ተናገሩ፡፡

መምህር ጋሻነው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ባህል ሆኖ እያንዳንዱን ዜጋ ሊያሳትፍ የሚገባ ስራ ነው።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎቱን በተጠናከረ አደረጃጀት እንዲመራ በማድረግ ከአንድ ወቅት ስራነት ባለፈ ዓመቱን ሙሉ የሚከናወን ልምድ አድርጎ መውሰድ ይገባል ብለዋል።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለሁሉም ሰው ማህበራዊ ኃላፊነቱ እንደሆነ በመገንዘብ እንደባህል አድርጎ መቀጠል ይገባል ያሉት መምህሩ፤ ትውልድ በመተሳሰብና በመረዳዳት አብሮ የመኖርን ባህል በማሳደግ የሰብዓዊነት ተግባራትን እንዲያጎለብት በማገዝ ረገድ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ጠቀሜታው የጎላ ነው ብለዋል።

ከበጎ ፈቃድ አገልግሎት ይበልጥ ተጠቃሚው የሚሆነው እራሱ የበጎ ፈቃድ የሚሰጠው አካል ነው ያሉት መምህር ጋሻነው፤ የግለሰቡን ችግር የመፍታት አቅም ያዳብርለታል፣ በማህበራዊ ሕይወቱ ደስተኛ እንዲሆን እና የውሳኔ ሰጪነትና መፍትሔ የማበጀት ክህሎቱ እንዲዳብር ትልቅ እድል ይፈጥርለታል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ መምህሩ ገለጻ ከሆነ፤ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ የተበረከተላቸው ሰዎች ደግሞ ከመንፈስ እርካታ ባለፈ የሚያስብልኝ ወገን አለ ብለው እንዲጽናኑ ዕድል ያገኛሉ። በተጨማሪ በቀሪው ዘመናቸው ለሀገርና ለህዝብ ጠቃሚ የሆነ ነገር መስራት እንዳለባቸው በቂ ግንዛቤ ስለሚወስዱ የማድረግ አቅሙን ባገኙ ጊዜ ጠቃሚ ስራ እንዲያከናውኑ አቅም ይፈጥርላቸዋል።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሲደረግላቸው የነበሩ ሰዎች ትልቅ የበጎ ፈቃድ ሰጪ ድርጅት ገንብተው አገልግሎት ሲሰጡ የሚታዩባቸው አጋጣሚዎች ከፍተኛ ናቸው። እንደአጠቃላይ እሳቤውን ካሳደግነው በጎ ፈቃድ ሀገርን በዘላቂነት ለመገንባት ያለው ሚና ጉልህ ነው ብለዋል።

መምህሩ አክለው እንዳስታወቁት፤ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ቀጣይነት እንዲኖረው ማህበረሰቡ፣ የበጎ ፈቃድ የሚሰጡ ማህበራትና የሚመለከታቸው ተቋማት በጋራ መስራት አለባቸው። በዘርፉም አመርቂ ስራዎችን ለመስራት ሀገር በቀል የበጎ ፈቃድ ድርጅቶችን ማበራከት ያስፈልጋል።

መንግስት፣የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ሲቪል ሰርቪስ ድርጅቶች እንዲሁም የመገናኛ ብዙሃን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲበራከትና በሀገር ግንባታ ላይ ያለውን ጠቀሜታ በማስረዳት ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ሊፈጥሩ ይገባል ብለዋል፡፡

ወጣቶች በትርፍ ጊዜያቸው የችግረኞችን ቤት በመገንባት፣ አረጋውያንን በመንከባከብ፣ የከተማዋን የተለያዩ አካባቢዎች በማጽዳትና በዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በዘላቂነት ለማከናወን ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ ጠቁመዋል።

እንደ መምህሩ ገለጻ፤ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ዜጎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸው እንዲጨምርና ንቁ የፖለቲካ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚያግዝ በመሆኑ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አስፈላጊነት ላይ ዕምነት ያለው ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚመለከታቸው ሁሉ ጥረት ሊያደርጉ ይገባል።

# የሥራ አጥ ቁጥርን ለመቀነስ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በተጨማሪም ኤጀንሲዎች ከሚገባቸው በላይ ክፍያ ባለመጠየቅ የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ሰላማዊ እንዲሆን እንዲሁም ሰራተኞች መብታቸውንና ግዴታቸውን አውቀው በሰሩት ልክ ገቢ እንዲያገኙ ማድረግ አለባቸው ሲሉ ተናግረዋል።

በዘርፉ የሚስተዋሉ ሰፊ ክፍተቶች እንዳሉ የገለጹት አቶ ንጉሱ፤ መንግሥትም ችግሮቹን ለመፍታት ከኤጀንሲዎች ጋር በቅርበት እንደሚሰራ አስታውቀዋል።

ምቹ የሥራ አካባቢዎችን መፍጠር እንዲቻል መንግስት አዳዲስ ደንቦችንና መመሪያዎችን በስራ ላይ እንደሚያውልም ተናግረዋል።

በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍም ተመሳሳይ የውይይት መድረኮች ቀጣይነት ባለው መልኩ ማካሔድ እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

በመድረኩ ጥናታዊ ጽሁፍ ያቀረቡት በሚኒስቴሩ የሀገር ውስጥ ስራ ስምሪትና ማስፋፊያ ኃላፊ አቶ ደጀኔ በቀለ በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ የስራአጥ ምጣኔው ስምንት በመቶ እንደሆነ ገልፀው፤ በከተማዎች የሚታየው የስራ አጥ ቁጥር ከገጠር ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር የሥራ አጥ ሴቶች ቁጥር ከፍተኛ መሆኑን ተናግረው፤ የግል አሰሪና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች የሴቶችን ስራ አጥነት በመቀነስ ረገድ ተጨማሪ ጥረት ማድረግ እንደሚገባቸው ጥሪ አቅርበዋል።

በየጊዜው ከዩኒቨርሲቲ የሚመረቁ ወጣቶች በሥራ አጥነት ችግር ላይ ሲወድቁ እንደሚስተዋል አንስተው፤ ኤጀንሲዎች ከተቋማት ጋር በትብብር በመስራት የችግሩን ግዝፈት የሚመጥን ጥረት ማድረግ እንደሚገባቸው ተናግረዋል።

አዲስ አበባ ከተማና አማራ ክልል ከፍተኛውን የኤጀንሲዎች ቁጥር እንደሚይዙ የተገለፀ ሲሆን፤ በዝቅተኛ ደረጃ ሀረር እና ሶማሌ ክልሎች ላይ በንጽጽር በቁጥር አነስተኛ የሆኑ ኤጀንሲዎች እንደሚንቀሳቀሱ አስታውቀዋል።

በቀጣይም ኤጀንሲዎች የተለዩ ችግሮችን ለመፍታት ከሰራተኞችና ከሌሎች አካላት ጋር በጋራ ለመስራት የሚረዳ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት እንደሚገባቸው ተጠቁሟል።

ከውይይቱ ተሳታፊዎች የተለያዩ ጥያቄዎች ተነስተው ውይይት የተደረገባቸው ሲሆን፤ መሻሻል የሚገባቸው የሕግ ማዕቀፎችን በአጠቃላይ ፈትሾ ማሻሻል፣ ከኤጀንሲ አደረጃጀቶች ጋር በጋራ የሚሰራበትና ቋሚ ግንኙነት እየተደረገ ስራዎች የሚገመገሙበትን ሥርዓቶች መዘርጋት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች መሆናቸው ተገልጿል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የስራ አጥ ቁጥር ችግሩን ለመቀነስ እስከ 2017 ዓ.ም ድረስ ኤጀንሲዎችን ጭምር በማስተባበር ለ14 ሚሊዮን ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር አቅዷል፡፡

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የ10 አመት ዕቅዱን ተግባራዊ እያደረገ ሲሆን፤ እስከ 2022 ዓ.ም ድረስ ለ20 ሚሊዮን ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር እየሰራ እንደሆነ አስታውቋል።

በምክክር መድረኩም የክልል የሥራና ክህሎት ቢሮ ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎችና ከተለያዩ የግል አሰሪና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲዎች የተወጣጡ ተወካዮች ተገኝተዋል።

# ክልሉ በሌማት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የቤኒሻንጉል ክልል የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ባበክር ኸሊፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በክልሉ በተለይ የሌማት ቱሩፋት ከተጀመረ ጀምሮ ከፍተኛ የንብ ማነብ ስራ ለማካሄድ ስራዎች ተጀምረዋል፡፡ የሌማት ቱርፋት ፕሮጀክት ከተጀመረ አንስቶ ከአንድ ሺህ በላይ የንብ ቀፎዎችን ለ10 መንደሮች ለማሰራጨት እቅድ ተይዞ ስራ ተጀምሯል፡፡

ከአንድ ሺህ ያህል የንብ ቀፎዎች ውስጥ 250 ያህሉ ለአርሶ አደሩ መሰራጨታቸውን የገለጹት ኃላፊው፤ አቅርቦት ላይ የተወሰኑ ተግዳሮቶች ቢኖሩም የዶሮ እርባታ ላይም ሥራዎች እየተሠሩ ነው ብለዋል፡፡ ለክልሉ ወጣቶች 26 ሺህ ዶሮዎች ተሰራጭተዋል ሲሉም ገልጸዋል፡፡

የሌማት ቱሩፋት በትንሽ ቦታ የገበሬውን ምርታማነት የሚያሳድግ እና ሀገሪቷ ውስጥ ያለውን የስራ አጥ ቁጥር መቀነስ የሚያስችል ነው ያሉት አቶ ባበክር፤ በቀጣይም በመርሃ ግብሩ በሙሉ አቅም ማምረት ሲጀመር ሀገሪቷ በምግብ እራሷን የመቻል ዋስትና የሚሰጥ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የሀገሪቱ መንግስት ለሌማት ቱሩፋት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ በመሆኑ ተጨባጭ ውጤቶች ሊመዘገቡ እንደቻሉ የተናገሩት ኃላፊው፤ በተመሳሳይ በቤኒሻንጉል ክልል የሌማት ቱሩፋት ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲደረግ መቆየቱን ጠቁመዋል፡፡

በመሆኑም በክልሉ የሌማት ቱሩፋት እንቅስቃሴ ከተጀመረ ወዲህ ሦስት መቶ ኩንታል የዓሣ ምርት መገኘቱን አስታውቀዋል። እንቅስቃሴው መልካም ጅማሮ የታየበት መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡

በክልሉ ከሚገኙ ከጉባ እና ከሰዳል ወረዳዎች ወጣቶችን በመመልመል በዓሣ ምርት ልማት ማሰማራት እንደተቻለ ተናግረው፤ ከሰንቀሌ እና ከአሶሳ ወረዳዎች የተውጣጡ ወጣቶች ደግሞ የዓሣ ምርቱን ተረክበው እንዲያከፋፍሉ ተደርጓል ብለዋል፡፡

# ዓድዋ ለዜጎች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ባህር አቋርጦ የመጣውን ቅኝ ገዥ አሸንፈው አገር ማስቀጠል የቻሉት አባቶች ሕብረት ስለነበራቸው ነው ያሉት ዶክተር አየለ፤ በተደራጀ መንገድ የአገራቸውን ህልውና ለማስጠበቅ በመፋለማቸው አርበኞቻችንን በአግባቡ ልናከብራቸውና ታሪካቸውን ልንዘክር ይገባል ብለዋል።

በየጊዜው መሰረተ ቢስ ጉዳዮችን እየያዝን እርስ በእርሳችን የምንጋጭበት ምክንያት የጥንቱን ታሪክ በአግባቡ ካለመረዳት የመነጨ ነው። በዚህ ረገድ ትውልዱ ስለአገሩ አንድነትና የተጋድሎ ታሪክ በቂ ዕውቀት እንዲኖረውና በስሜት እንዳይነዳ የሚያደርግ ግንዛቤ ሊፈጠርለት ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ጣሊያኖች ለተሸነፉት የጦር ጄኔራሎች በርካታ ጽሁፍና ማስታወሻዎችን አስቀምጠዋል። በአንጻሩ ኢትዮጵያውያን ግን ለአሸናፊዎቹ አርበኞቻችን ያበረከትነው ማስታወሻና የፈጠርነው ግንዛቤ በቂ አይደለም። የዓድዋ ድል በተቀናጀ አገራዊ አንድነትና የጀግንነት ስሜት የመጣ መሆኑን አስረግጦ የሚያስረዳ ስርዓት ሊኖረን ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

በትናንሽ ነገሮች እንድንባላ የሚፈልጉ አካላትን ማሸነፍ የምንችለው እንደአድዋ ድል ያሉ ትልልቅ የታሪክ ምዕራፎችን በአሁኑ ትውልድ ላይ እንዲሰርጽ በማድረግ ነው። በተለይ ጦርነቱ እንዴት እንደተደረገና እንዴት ባለ ህብረብሔራዊ ስሜት እንደታለፈ የሚያሳዩ ሁነቶችን በማዘጋጀት፣ በመጽሐፍና በፊልም እንዲሁም በሙዚቃዎች ጭምር በማሳየት ሕዝብን ማሳወቅ ይገባል ብለዋል።

በመገናኛ ብዙሃን፣ በማህበራዊ ሚዲያዎችና በተለያዩ ሁነቶች ላይ የሚከናወኑ የዓድዋ ድል ዝክሮች ወጣቱን እያነቃቁ በመሆኑ ይበልጥ ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

ለአገር ግንባታ የላቀ አስተዋጽኦ የሚያበረክተው የዓድዋ ድል ለጥቁር ሕዝቦችም ነጻነት የሚተርፍ የታሪክ ማስረገጫ ያለው ድል በመሆኑ በአህጉር አቀፍ መድረኮች ጭምር ድሉን የሚያስተጋቡ ስራዎች ያስፈልጋሉ ብለዋል።

የአሁኑ ማንነታችንና ነጻነታችን በአድዋ ድል ላይ እንደመገንባቱ የአባቶቻችንን ድል ጠብቀን ለትውልድ ማስተላለፍ አለብን። 127ኛውን የዓድዋ ድል ለአገራቸው ነጻነት ሲሉ የተሰውና የተጋደሉ አርበኞችን በተገቢው መንገድ በማሰብ አንድነታችንን ሊያጠናክር የሚችል ስራ ማከናወን ይገባል ሲሉ አስታውቀዋል።

# የዓድዋ ሙዚየም...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ያላቸው ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ በ2015ዓ.ም አምስት ነባርና ስድስት አዳዲስ ፕሮጀክቶችን እያስገነባ ይገኛል። የዓድዋ ፕሮጀክትም አንዱ ሲሆን፤ ይህ ፕሮጀክት የጥቁር ህዝቦች ጀግንነት የድል መነሻና ኢትዮጵያዊ አንድነት ተምሳሌት ነው። ፕሮጀክቱ የአድዋን ታሪክ በሰፊው ለመግለጽና፣ ለሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ርቀት መለኪያ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ እየተገነባ ይገኛል።

ዳይሬክተሩ፤ ለዓድዋ ፕሮጀክት ግንባታ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ሙሉ በሙሉ ከውጪ የሚገቡ በመሆናቸው በኮቪድ ምክንያት የግብዓት ሎጀስቲክ ሰንሰለቱ ችግር እንደነበረበት ገልጸዋል። ሆኖም ከቻይና ኤምባሲ ጋር በመነጋገር ችግሩ እንደተፈታና አሁን ላይ በከፍተኛ ፍጥነት እየተሰራ እንደሆነ አመላክተዋል። በአሁኑ ወቅትም የፕሮጀክቱ "ፊዚካል" አፈጻጸም 78 ነጥብ 2 በመቶ መድረሱንና በሚቀጥለው ዓመት ጥቅምት ወር ሙሉ ለሙሉ ተጠናቅቆ ወደ ሥራ እንደሚገባ አስታውቀዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ፕሮጀክቱ የዓድዋ ሙዚየም ማዕከል ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን፤ ሲጠናቀቅ የዓድዋ ጦርነት ከመጀመሩ አስቀድሞ ጦርነቱ እስከተካሄደበት፣ በወቅቱ የነበረውንና እስካሁን ያለውን ታሪክ የሚገልጽ፣ የወደፊቷ ኢትዮጵያ ምን ትመስላለች የሚለውን የሚያስቃኝ ፕሮጀክት ነው። በውስጡም የትራንስፖርት ተርሚናል፣ ሲኒማ ቤት፣ የመሰብሰቢያ አዳራሾች፣ ካፍቴሪያ፣ ከአንድ ሺህ በላይ መኪና ማቆሚያ ስፍራ፤ የሙዚየሙን ሁኔታ የሚገልጹ የሥነ ጥበብ ሥራዎችን ያካተተ ነው።

ሙዚየሙ የዓድዋን ሰንሰለታማ ተራሮችን፣ ፈረሰኞችን ፣ ለሴት ጀግኖች ክብር የተሰየመ ማስታወሻዎችን፣ የተሰው ሰማዕታትን የሚዘክር፣ የአንድነት ማዕከል፣ የአፍሪካ ነፃነት ማስታወሻ እንዲሁም የኢትዮጵያ ጀግኖች ጉዞን የሚያሳዩ የሥነ ጥበብ ሥራዎች እንደሚኖሩትም ዳይሬክተሩ ጠቅሰዋል።

ከዚህም ባሻገር የዘውዲቱ ሆስፒታል ማስፋፊያ፣ የትራንስፖርት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት፣ የሾላ መኪና ማቆሚያ ፕሮጀክት፣ የገበያ ማዕከላት፣ ለ20ሺህ ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር የሚያስችል የኢንዱስትሪ ማዕከል፣ የሴቶችን አቅም ግንባታ የሚያሳድግ "የሴቶች ተሃድሶና መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት" በታቀደላቸው ጊዜ ግንባታቸው እየተከናወነ እንዳለም አክለው ገልጸዋል።

ሜጋ ፕሮጀክቶች በኮቪድና በጦርነቱ ምክንያት ሥራቸው ሳይቋረጥ እየተሰሩ መቆየታቸውንና በ11 ፕሮጀክቶች ለ16 ሺህ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠራቸውንም ዳይሬክተሩ ጨምረው ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ዓድዋ፦ የአንድነት፣ የጀግንነትና የጽናት ምሳሌ!

እኛ ኢትዮጵያውያን በየዘመኑ ከፍያሉ መስዋዕትነቶችን የጠየቁ ተጋድሎዎችን በማድረግ የነፃነታችን ባለቤት በመሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ የገዘፈ ታሪክ ባለቤት መሆን የቻልን ሕዝቦች ነን። ይህ የተጋድሎ ታሪካችን ከእኛም አልፎ በአፍሪካና ካረቢያን የሚገኙ ጥቁር ወንድሞቻችን የአልገዛም ባይነትን መንፈስ አምጠው እንዲወልዱ ሁነኛ የአቅም ምንጭ ሆኗቸዋል፤ ዛሬ ላይ ለሚያጣጥሙት ነፃነታቸውም ፈር ቀዳጅ መሆናችን የተረጋገጠ ነው።

የዓድዋ ድል ከነዚህ የነፃነት የተጋድሎ ታሪካችን ውስጥ በዋነኛነት የሚጠቀስ ነው። በጥቁር ሕዝቦች ታሪክ ውስጥም እንደ አንድ ታላቅ ዓይን መግለጫ ክስተት፤ የአይቻልምን የገዘፈ ቀንበር ከጥቁር ሕዝቦች ትከሻ ላይ አሽቀንጥሮ መጣል የሚያስችል መነቃቃትን የፈጠረ፤ ለእነዚህ ሕዝቦች የአዲስ የነፃነት ትግል ታሪክ ምዕራፍ መከፈቻ ተደርጎ የሚወሰድ ነው ።

ኢትዮጵያውያን ለአገራቸው ካላቸው ጥልቅ ፍቅር የተነሳ ዘር እና ሃይማኖት ሳይለያቸው ቀፎው እንደተነካበት ንብ በአንድነት በመንቀሳቀስ ስለአገራቸው ከፍ ያለ መስዋዕትነት በመክፈል የቀደሙ አባቶች በብዙ መስዋዕትነት ያቆይዋትን በነፃነቷ የተከበረች አገር በሌላ ተጨማሪ የተጋድሎ ታሪክ ለመጪው ትውልድ ማስረከብ የቻሉበት ነው።

ጥልቅ የአገር ፍቅር ስሜትና ከዚህ የሚመነጭ ለአገር መስዋዕት ሆኖ የማለፍ መነቃቃት የታየበት የዓድዋው ጦርነት፤ ሁኔታዎች ወራሪው ኃይል እንዳሰበው ሳይሆን መልካቸው ተቀይሮ ዓለም አቀፍ አጀንዳ እንዲሆኑ ያደረገና ዓለም ስለ ጥቁር ሕዝቦች የነበረውን የተሳሳተ አመለካከት መልሶ እንዲያጤነው አስገዳጅ ሁኔታ መፍጠር ያስቻለ ነው።

ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያውያን በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑምና ማንም ወራሪ የቱንም ያህል የገነገነ ቢሆን፤ ለነፃነታቸው ካላቸው ቀናኢነት አንጻር፤ ነፃነታቸውን ከእጃቸው ፈልቅቆ ማውጣት በቀላሉ የማይታሰብ መሆኑን ከፍ ባለ የተጋድሎ መስዋዕትነት ያሳየ፤ ለዚህ የሚሆን አዲስ የታሪክ ትርክት የፈጠረ ነው።

ኢትዮጵያውያን ለአገር በሆነ ጉዳይ ለሚቀርብ ብሔራዊ ጥሪ ጨርቄን ማቄን እንደማይሉ፤ በየትኛውም ሁኔታ ለኢትዮጵያውያን ለአገር መሞት ትልቅ ክብር እንደሆነ በወቅቱ የነበረው ትውልድ በተግባር ማሳየት እንዲችል ያደረገ፤ በዚህም ጉዳይ ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ከታሪክ ባለፈ ተጨባጭ ማኅበረሰባዊ እውነታውን በዓይኑ መታዘብ የቻለበትን ዕድል የፈጠረ ነው።

መላው የአገሪቱ ሕዝብ ለነፃነቱ ካለው ቀናኢነት የተነሳ ከነበረው የጦርነት ተሳትፎ ጎን ለጎን፤ ጦርነቱ የተመራበት አገር በቀል ስትራቴጂ በርግጥም ኢትዮጵያውያን ጦርነትን የመምራትና በድል የማጠናቀቅ አቅም ባለቤት መሆናቸውን በአደባባይ መመስከር ያስቻለ ነው። አገሪቱን በኃይል ለማንበርከክ የሚደረጉ ጥረቶች ዋጋ እንደሚያስከፍሉም በተግባር ማሳየት ያስቻለ ክስተት ነው።

ይህ የሕዝባችን ፍጹም አንድነት የታየበት፤ አንድነት የድል መሠረት መሆኑ በተጨባጭ ትልቅ አገራዊ ተሞክሮ የሆነበት የዓድዋ ጦርነትና በጦርነቱ የተገኘው ድል፤ ዛሬም ድህነትን አሸንፈን የበለጸገች አገር ለመመስረት ለምናደርገው እልህ አስጨራሽ ትግል ትልቅ ተሞክሮ ስለሚሆን ከዚህ ድል ዛሬ ላይ ብዙ ልንማር እንደምንችል ይታመናል።

አባቶቻችን በብዙ መስዋዕትነት ያስረከቡን ነፃነታችን በዚህ ዘመን ከሚኖረው ያልተሟላ ትርጉም አንጻር፤ ይህንን ነፃነት ምሉእ ለማድረግ የጀመርነውን ድህነትን አሸንፎ የመውጣት እልህ አስጨራሽ ትግል በዓድዋ አባቶቻችን እንዳደረጉት ሁሉ ጨርቄን ማቄን ሳንል ተቀብለን ለመጪው ትውልድ የተሟላ ነፃነት የማስረከብ ኃላፊነታችንን ልንወጣ ይገባል።

ዛሬ ላይ አገራዊ ነፃነታችንን የተሟላ በማድረግ በዓለም አቀፍ መድረኮች አንገታችን አቅንተን፤ በልበ ሙሉነት ለመመላለስ፤ መንግሥት ድህነትን ለማሸነፍ ያቀረበውን አገራዊ ጥሪ መቀበል፤ ለዚህ የሚሆን ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት መፍጠር ይጠበቅብናል።

በአጠቃላይ ኅብረብሔራዊ አንድነታንን በማጽናት የዓድዋው ድል ቀጣይ የሆነውን የኢኮኖሚ ድል በተባባረ ክንድ እውን በማድረግ እንደቀደመው ዘመን ለሌሎች ወንድሞቻችን የይቻላል መንገድን ማመላከት ከአሁኑ ትውልድ የሚጠበቅ አገራዊ ኃላፊነት ነው።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ወጣቱ የአባቶቹን አሻራ ማስቀጠል ይጠበቅበታል

ክብረአብ በላቸው

ወቅቱ አውሮፓውያን አፍሪካን በቀኝ ግዛት ስር ለማድረግ ዓይናቸውን ወደ አህጉሪቱ ያማተሩበት የታሪክ ምዕራፍ ነበር። በወቅቱ አብዛኞቹ የአፍሪካ አገራት በአውሮፓውያን እጅ ሲወድቁ፣ ኢትዮጵያን ለመውረር ቀይ ባሕርን ያቋረጠችው ጣሊያን ግን ዕቅዷ ሳይሳካላት ቀርቷል።

በ1888 ኢ.ም (ከ1895 እስከ 1896 እ.ኤ.አ.) ዓድዋ ላይ የጣሊያንን ጦር የገጠመው የኢትዮጵያ ሰራዊት ድል ማስመዝገቡ፣ ድሉ የአፍሪካ ብሎም የመላው ዓለም ጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ድል መሆኑ ሲታወቅ፤ ጣሊያን የሽንፈት ፅዋ ተጎንጭታ የኢትዮጵያን ምድር ለቃ ወጥታለች።

ነገር ግን በዚህ በዓድዋ ሽንፈት ቂም የቋጠረችው ጣሊያን ከአርባ አመታት በላይ የጦርነት ድግስ በኋላ ዳግም ተመልሳ በመምጣት በኢትዮጵያ ላይ በዓለም አቀፍ ሕግ በተከለከሉ የጦር መሣሪያዎች ሳይቀር በመጠቀም በኢትዮጵያውያን ላይ ወረራ አካሂዳለች።

በወቅቱም ኢትዮጵያ ለዓለም መንግሥታት ማህበር (League of Nations) ወረራው ተገቢ አይደለም ብላ አቤት ብትልም አጋርነት ካሳዩ ጥቂት አገራት ውጪ ሰሚ አላገኘችም ነበር።

የመንግሥታቱ ማህበር ከተመሠረተ ከአምስት ዓመታት በኋላ የተካሄደውን ይህን ወረራ ለመቀልበስ / ለአምስት አመታት/ የኢትዮጵያ መንግሥትና መላው ሕዝብ ታላቅ ተጋድሎ አድርገዋል።

ከዚህ ወስጥ የየካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ክስተት አንዱ ነው። በዕለቱ ለኢጣሊያ ንጉሣዊ ቤተሰብ አንድ ልዑል በመወለዱ ምክንያት በጄነራል ግራዚያኒ ትዕዛዝ በቀድሞው የገነተ ልዑል ቤተመንግሥት /በአሁኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ/ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች፤ ለፋሺስቶቹ ያደሩ ከሀዲ ባንዳዎችና መኳንንት፤ የፋሺስት ባለሥልጣናትና ወታደሮች እንዲሰበሰቡ ተደርጎ ነበር።

ከተሰብሳቢዎቹ ጋር ሰርገው የገቡት አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም ለፋሺስቶቹ ባደሩ ከሀዲ ባንዳዎችና መኳንንቶች፤ እንዲሁም በፋሺስት ባለሥልጣናት ላይ የእጅ ቦምቦችን በመወርወር ጉዳት ማድረሳቸውን ተከትሎ ጭፍጨፋው ከግቢው ተጀምሯል።

በዕለቱ በግቢው ውስጥ የነበሩ ከሦስት መቶ በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ተጨፈጨፉ፤ የተማሩ ወጣቶች፣ የጦር መኮንኖችና ካህናት፣ መነኮሳት በሙሉ ከከተማው እየተለቀሙ እንዲጨፈጨፉ ተደረገ። የከተማዋ ነዋሪዎች እቤት ውስጥ እንዲገቡ እየተደረገ ከውጭ ተቆልፎባቸው ቤንዚን እየተርከፈከፈ በእሳት እንዲቃጠሉ ሆነ።

ኢትዮጵያውያንን በአካፋ፣ በዶማ፣ በመጥረቢያ በተገኙበት እየቆራረጡ አዲስ አበባን በደም ጎርፍ እንድትጥለቀለቅ ሆነ። ፋሽስቶች በሦስት ቀናት ውስጥ ብቻ ከአዲስ አበባንና አካባቢዋ ከ30ሺህ የሚበልጥ ሕዝብ ፈጁ።

የበቀል እርምጃው በአዲስ አበባ ብቻም ሳይሆን አብርሃ ደቦጭ፤ ሞገስ አስገዶምና አባሪዎቻቸው ተሸሸገውበታል ወደ ተባለው፣ ደብረሊባኖስ ገዳምም ደርሶ ቀሳውስትና ምዕመናን እንዲገደሉ ተደረገ። በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አሰቃቂና አሳዛኝ ከሆኑት ጭፍጨፋዎች መካከል አንዱ የሆነው የየካቲት 12 ጭፍጨፋ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ከነበሩ አስከፊ ክስተቶች መካከል ይጠቀሳል።

በጊዜው ኢትዮጵያውያንን ለዚህ ሁሉ ግፍ እና በደል የዳረጋቸው የሰሩት ጥፋት ኖሮ ሳይሆን በአንገዛም ባይነታቸው ብቻ በወራሪ ኃይሎች እንደ በደል ተቆጥሮ ነበር። ይህ አሰቃቂ ክስተት ከተፈጠረ ዘንድሮ ሰማንያ ስድስተኛ ዓመቱን በአዲስ አበባ ስድስት ኪሎ በሚገኘው የሰማእታቱ መታሰቢያ ሀውልት የአበባ ጉንጉን በማስቀመጥ ታስቦ ውሏል።

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን በዘመናት ሁሉ ለነፃነት እና ለፍትህ የከፈሉት ዋጋ እጅግ ብዙ ነው። ዘመናዊ መሣሪያ እስከ አፍንጫው የታጠቀን ጦር በአንድነታቸው ተማምነው፣ በጊዜው ኋላ ቀር በሆነ መሣሪያ ይዘው፣ በአይበገሬነት ተፋልመው ጠላትን መርታት ችለዋል።

ዛሬ ላይ በቀድሙት አባቶቻችን ዘንድ የነበረው አንድነት እና ህብረት ከብዙዎቻችን ላይ እየጠፋ፣ ወይም እየቀነሰ ስለመሄዱ በብዙ መልኩ እንታዘባለን። የአሁኑ ትውልድ የቀደመ የአገሩን አኩሪ ባህልና ታሪክ የዘነጋ ሁሉ እስኪመስል ድረስ ሁኔታዎች አሳሳቢ እየሆኑ ነው።

**ታዲያ ዛሬ አገሪቱን እና ሕዝቦቿን ከያዟት የድህነት አረንቋ ማውጣት እና የቆየ መጥፎ ገፅታዋን መቀየር የዚህ ትውልድ የቤት ሥራ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ እውነት ነው**

ለአገርና ሕዝብ እዚህ ግባ የሚባል ፋይዳ በሌላቸው ጉዳዮች ተጠምዶ ሲውል እናያለን። ዛሬ ዘመን ተቀይሯል። የአሁኑ ትውልድ ተጋድሎ ማሸነፍ የሚጠበቅበት ግን ደህነትን እና ኋላ ቀርነትን ነበር።

የቀደሙ አባቶቹ በዘመናቸው የገጠማቸውን እና “ባሪያ ላድርግህ” ያላቸውን ጠላት ተዋግተው ድል በማድረግ ዛሬ ላይ ልጆቻቸው በኩራት የሚናገሩትን ታሪክ መፃፍ ችለዋል።

ታዲያ ዛሬ አገሪቱን እና ሕዝቦቿን ከያዟት የድህነት አረንቋ ማውጣት እና የቆየ መጥፎ ገፅታዋን መቀየር የዚህ ትውልድ የቤት ሥራ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ እውነት ነው። ነገር ግን፣ ዛሬም ኢትዮጵያን በዓለም ማህበረሰብ ፊት አንገት ያስደፋትን ድህነት እና ኋላቀርነት ማሸነፍ አልቻለችም።

ሰፊ እና ለእርሻ ተስማሚ የሆነ ድንግል መሬት፣ የተፈጥሮ ሀብት፤ እንዲሁም ሰፊ ቁጥር ያለው አምራች የሰው ኃይል ይዛ ዛሬም በድህነት የመዳከሯ ምክንያት በዋናነት በአሁኑ ትውልድ ያለ ደካማ የሥራ ባህል እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ።

የዚህ ዘመን ትውልድ ባለፈ እና የእርሱ አሻራ ባልሆነ የስልጣኔ እና የገድል ታሪክ ብቻ መኩራራትን ሥራው አድርጎ፤ ለአገር በማይበጁ ጥቃቅን ጉዳዮች ተጠምዶ ጊዜውን እያጠፋ ካለፉት አባቶቹ በአደራ የተረከባትን አገር ዛሬም ሰቅዞ ከያዛት ድህንነት እና ኋላቀርነት ማውጣት አልቻለም።

አገር የሚገነባው በትውልድ ቅብብሎሽ፣ ያለ መሰልቸት በሚሠራ ሥራ እንደሆነ እሙን ነው። የዛሬው ትውልድ እርሱ በኩራት እንደሚያወራላቸው፣ እንዳለፉት አባቶቹ በመልካም ለመነሳት (ስም ከመቃብር በላይ እንዲሉ) ብቻ ሳይሆን፤ በሚመጣው ትውልድ በመጥፎ ታሪኩ ላለመወቀስ ብሎም በጀግኖች የሕይወት መስዋዕትነት የቆየች አገሩን ከያዛት ድህነት ለማላቀቅ፤ ብሎም ኃላፊነት እና አደራውን ለመወጣት መሥራት እንደሚጠበቅበት አያጠያይቅም እላለሁ። የአባቶቹን አሻራ ማስቀጠል ከወጣቱ ይጠበቃልና!!!

# ነፃ ሃሳብ

## ከምግብ በላይ የሆነው ስንዴ

እስማኤል አረቦ

ስንዴ ከሩዝ ቀጥሎ በዓለማችን በስፋት የሚመረት የሰብል ዓይነት ነው። በዓለማችን በድሃም ሆነ በሀብታም አገራት እጅግ ተፈላጊ የሆነ ሰብል ነው። ከምግብነት ባሻገርም ለአገራት ሰፊ የውጭ ምንዛሬን በማስገኘት በኩልም ሚናው ላቅ ያለ ነው። ለዚህም ይመስላል በርካታ አገራት ለስንዴ ከምግብ በላይ የሆነ ግምት የሚሠጡት።

በዓለም ላይ በስንዴ አምራችነታቸው ከሚታወቁ አገራት ውስጥ ቻይና፤ ሕንድ። ሩስያና ዩክሬን ግንባር ቀደሞቹ ናቸው። ቻይና የዓለማችን ቁጥር አንድ ስንዴ አምራች አገር በመሆን በአመት 2 ነጥብ 4 ቢሊዮን ቶን የምታመርት አገር ነች። ይህም የዓለማችንን 17 በመቶ የስንዴ ምርት የሚሸፍን ነው።

ካላት የሕዝብ ብዛት አንጻር ግን የምታመርተውን ሁሉ ለአገር ውስጥ ፍጆታ ታቀርባለች፤ በዚህም ታላቋ ስንዴ ተመጋቢ አገርም በመሆን ትታወቃለች። ስንዴ በስፋት በማምረቷ ሕዝቦቿን በቀላሉ መመገብ ችላለች። ከተረጂነት ተላቃም በምግብ እህል እራሷን በመቻል ከስንዴ ፖለቲካ እራሷን መታደግ ችላለች።

ሌላኛዋ ስንዴ አምራች አገር ራሺያ ናት። ራሺያ ስንዴ የውጭ ንግዷ መሠረት አድርጋም ትወስዳለች። 8 ነጥብ 4 በመቶ የሆነውን የዓለማችንን የስንዴ ምርት የምትሸፍን ሲሆን፣ ከዚህ ምርቷም 7 ነጥብ 3 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ታገኛለች። ከምርታማነቷና ከምታገኘው ገቢ (ዶላር) ባሻገርም በምግብም እራሷን የቻለች፤ በስንዴ ፖለቲካ ነፃነቷን ማስከበር የተሳካላት አገር ለመሆን በቅታለች።

ዩክሬን ዓለምን በስንዴ እህል በመመገብ ትልቅ ስምና ዝና ያተረፈች አገር ነች። ከአመት በፊት ከሩሲያ ጋር በገባችበት ጦርነት ምክንያት እንኳን 3 መቶ ሺህ ቶን ስንዴ እና በቆሎ እንደተበላሸባት መግለጿ የሚታወስ ነው። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዩክሬንን ስንዴ በዋነኝነት ገዥ ሲሆን፤ የገዛውንም ስንዴ አፍሪካን ጨምሮ በመላው ዓለም በረሃብና በተለያዩ አደጋዎች ውስጥ ለሚገኙ አገራት ዜጎች ያከፋፍላል።

ኢትዮጵያ ለዘመናት ያህል ነፃነቷን ጠብቃ የኖረች የጥቁር ሕዝቦች ተምሳሌት ብትሆንም በምግብ ሰብል እራሷን ባለመቻሏ ነፃነቷን የተሟላ ማድረግ ተስኗት ቆይቷል። በአድዋ የተገኘው ድል በቅኝ ገዢዎች የፈረጠመ ኢኮኖሚ ሲጠመዘዝ ኖሯል። የኢትዮጵያ ኩራትና ድል በስንዴ ልመና ኮስሶ በዓለም መድረኮች ሁሉ ለምናቀርበው ጥያቄና ለምናሰማው ድምጽ መጀመሪያ ሆዳችሁን ሙሉ የሚል ምላሽን ሲነገረን ኖረናል።

ዛሬ ግን የአድዋ ድል በተገቢው ቦታው ላይ እንዲነግስ የሚያስችል አኩሪ ታሪክ መጻፍ የምንችልበት ደረጃ ላይ የደረስን ይመስላል። ኢትዮጵያ ዳግም ነፃነቷን ልታውጅ እሷም እንደነዩክሬን በስንዴ ምርት ራሷን ችላ ወደ ውጭ ገበያ ልትልክ፤ ከስንዴ ለማኝነት ወደ ስንዴ ላኪነት ልትሸጋገር ዳር ዳር እያለች ነው።

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ስንዴ ሸማች ከሆኑ አገራት ውስጥ በግንባር ቀደምትነት የምትታወቅ ስትሆን በየአመቱም እስከ 107 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ በማስገባት 1 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ወጪ ታወጣለች። ይህንን እውነታ ለመቀልበስ በተደረገው ርብርብ /ባለፉት አራት አመታት መንግሥት ለስንዴ ምርት በሰጠው ትኩረትም ኢትዮጵያ ስንዴን ከውጭ ማስገባት ከማቆሟም ባሻገር ወደ ውጭ መላክ ጀምራለች።

ኢትዮጵያ ከስንዴ ተቀባይነት ወደ ስንዴ ላኪነት እራሷን በመለወጥም ታሪክ እየሠራች ነው፤ ይህ ለቀጣናው አገራት ኩራትና ተስፋ፤ ሠርቶ የማሠራት ተምሳሌትም ያደርጋታል። ጥረቷ በታሰበው ልክ ከተሳካም አገሪቱ በዓለም ስንዴ በማምረት ተጠቃሽ ከሆኑ 18 አገራት ተርታ ያሰልፋታል።

በተያዘው አመት ኢትዮጵያ 129 ሚሊዮን ኩንታል የሚጠጋ የስንዴ ምርት ታመርታለች ተብሎ ይጠበቃል። 97 ሚሊዮን ኩንታል የሚሆን ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚውል ሲሆን 32 ሚሊዮን የሚጠጋው ወደ ውጭ ተልኮ ዶላር የሚያስገኝ ነው። ለዚህም ዘንድሮ ሱዳንና ኬንያን ጨምሮ ስንዴ የመግዛት ፍላጎት ያላቸው ስድስት አገራት ጋር የ3 ሚሊዮን ኩንታል የውል ስምምነት ተፈርሟል።

የረድኤትና ሌሎች የአገር ውስጥ ድርጅቶች ከውጭ የሚገዙትን ስንዴ ምርት በአገር ውስጥ እንዲተኩ በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል የ2 ነጥብ 9 ሚሊዮን ኩንታል የውል ስምምነት በመፈረም ላይ መሆናቸውም ተሰምቷል። በዚህም ኢትዮጵያ ከ200ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ እንደምታገኝ ይገመታል።

ይህ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ከማሳደግ ባሻገር የጎረቤት አገራት ከአውሮፓ፣ ከአሜሪካና ካናዳ ደጅ ጠንተው የሚገዙትን ስንዴ ከደጃቸው በቀላሉ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። የምሥራቅ አፍሪካን አካባቢም ከግጭትና ሁከት በማውጣት አገራቱን በልማት እንዲተሳሰሩ በር ይከፍታል።

ኢትዮጵያ በምግብ እህል ራሷን መቻል አቅቷት ቢሊዮን ዶላር አውጥታ ከውጭ ከማስገባት በዘለለ፣ ለዕርዳታ የብዙዎችን በር ስታንኳኳም ሰንብታለች። አንዳንድ ጊዜም ረጂ አገራት ስንዴን እንደመያዣ አድርገው የሚፈልጉትን ሁሉ ለመጫን ሲሞክሩ ታይተዋል። ሆኖም ይህ ታሪክ ዘንድሮ ያበቃ ይመስላል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) «ስንዴ አምርተን ከራሳችን አልፈን ወደ ውጭ እንልካለን» ብለው ሲናገሩ ብዙዎች ንግግሩን ከፖለቲካ ፍጆታነት የሚያልፍ አልመሰላቸውም ነበር። ሆኖም ንግግሩን በጥርጣሬ የተመለከቱት ሁሉ ዛሬ ምስክርነታቸውን መስጠት ጀምረዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ ርዕይ ግቡን መምታቱን ከአገሪቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናትና ከዘርፉ ባለሙያዎችም አልፎ በአሜሪካ የውጭ ግብርና ቢሮም ‹‹በኢትዮጵያ የስንዴ ምርት ትልቅ እመርታ እያሳየና ምርታማነቱ እየጨመረ ነው›› ተብሎለታል።

በአገሪቱ ዓምናና ዘንድሮ ስንዴ የተሸፈነው መሬት 2ነጥብ8 ሚሊዮን ሔክታር ነው፤ በበጋ ወቅት ይመረታል ተብሎ የታሰበውን 50 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴን ሳይጨምር ከ108 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል።

ስንዴ ለኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ ብቻ ሳይሆን በአገር ውስጥ ያሉ ኢንዱስትሪዎች እንዲነቃቁ የሚያስችል ሞተር ነው። የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል እንደተናገሩትም፤ የስንዴ ልማቱ በአገር ውስጥ ላሉ ከ440 በላይ ኢንዱስትሪዎች ግብዓትን ሙሉ በሙሉ በአገር አቅም መሸፈን የሚያስችል ነው። ከዚህም ባለፈ ስንዴን በጥሬው ብቻ ሳይሆን እሴት ጨምሮ ፓስታ፣ ማካሮኒና የመሳሰሉትን ምርቶች በማቀነባበር ወደ ውጭ ለመላክ ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ በትኩረት እንደሚሠራበት ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ስንዴን ለውጭ ገበያ አቅርባለሁ ስትል፣ ዘገባው በጣም የተጋነነና ከሁኔታዎች ጋር ያልተገናዘበ ነው በማለት የኢኮኖሚ ባለሙያዎች አስተያየታቸውን ሰጥተው ነበር። ከዚህም አንፃር የኢትዮጵያ የምግብ እጥረት ችግር የማይፈታ ነው ብለው የሞገቱም ነበሩ። ሆኖም ኢትዮጵያ የተናገረችውን እውን ማድረግ ችላለች። ይህንኑ አስመልክተውም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ‹‹ኢትዮጵያ ከስንዴ እርዳታ መላቀቅና ወደ ውጭ መላክ አትችሉም ያሉንን ችለን በማሳየታችን ኩራት ተሰምቶናል›› ብለዋል።

በሁሉም የአገሪቱ ክፍል የሚመረት ቢሆንም በዋናነት ስንዴ በኦሮሚያና በአማራ ክልል በስፋት ይመረታል። በአገሪቱ ከሚመረተው የስንዴ ምርት ውስጥ 54 ነጥብ 4 በመቶ ከኦሮሚያ የሚገኝ ሲሆን 27 በመቶ ከአማራ፤ 8ነጥብ 7 በመቶ ከደቡብ ሕዝቦች እንዲሁም 6ነጥብ 2 በመቶ ከትግራይ የሚገኝ ነው።

መንግሥት ለዘርፉ በሰጠው ትኩረትም የሶማሌ፣ የቤኒሻንጉል፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ሲዳማን እና የመሳሰሉት ክልሎች ኃይላቸውን አስተባብረው ስንዴን ማምረት ጀምረዋል። የእነዚህ አካባቢዎች ምርታማነት ሲጨምርም ኢትዮጵያ በአፍሪካም ሆነ በዓለም ላይ ያላት ስንዴን የማምረት ታሪክ በእጅጉ የሚቀይረው ይሆናል።

አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ እንኳን ኢትዮጵያ በአፍሪካ ከደቡብ አፍሪካ ቀጥላ ሁለተኛዋ ስንዴ አምራች አገር ለመሆን በቅታለች። የአፍሪካ አገራት ስንዴን ከውጭ በመቀበል የሚታወቁ ናቸው። ስንዴንም ለማግኘት በርካታ ውጣውረዶችን ማለፍ ይገባቸዋል። በዩክሬንና በራሽያ ጦርነትም በግልጽ እንደታየው በዓለም ላይ በሚነሱ መስተጓጎሎች የቅድሚያ ተጠቂዎቹ የአፍሪካ አገራት ናቸው። በዩክሬንና በራሽያ ጦርነትም በተከሰተው የስንዴ እጥረት እስከ 300 ሚሊዮን የአፍሪካ ሕዝብ ለርሃብ እንደሚጋለጥ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ግዙፍ ሚዲያዎቻቸው ጭምር በስፋት የዘገቡት ነው።

ኢትዮጵያ ስንዴ አምራችና ላኪ አገር መሆኗ በስጋት ውስጥ ላሉት የአፍሪካ አገራት ትልቅ እፎይታን ይዞ የሚመጣ ነው። ይህንኑ ሃቅ መሠረት በማድረግም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶክተር) በአፍሪካ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ250 ሚሊዮን በላይ እርዳታ ፈላጊዎች መኖራቸውን በመጥቀስ ‹‹ኢትዮጵያን ኤይድ›› በሚል ስንዴ ለመለገስ ተግተን እንሠራለን ነው ያሉት። በዓለም ላይ የተፈጠረውን የስንዴ ገበያ ችግር ለማቃለልም ኢትዮጵያ የበኩሏን እንደምትወጣ ገልጸዋል።

“ Index box market intelligence ” የተሰኘ የመረጃ መረብ ይፋ እንዳደረገውም፤ የአፍሪካ አገራት የስንዴ ፍላጎት እየጨመረ ነው። እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2012 ብቻ የአፍሪካውያን የስንዴ ፍላጎት በ1 ነጥብ 3 በመቶ ጨምሯል። ይህ አሃዝ በቀጣዮቹ አመታት እንደሚጨምር የመረጃ መረቡ ትንበያውን አስቀምጧል። ይህ ደግሞ እንደኢትዮጵያ ላሉ ስንዴ አምራችና ላኪ አገራት ጥሩ ዕድል ይዞ የሚመጣ ነው።

ወደ አፍሪካ ከሚገባው ስንዴ ውስጥ 50 በመቶ የሚሆነውን ምርት የሚወስዱት ናይጄሪያ፣ አልጄሪያና ግብጽ ናቸው። የጎረቤታችን ኬንያ ፍላጎትም በየጊዜው እየጨመረ መጥቷል። ዘንድሮም ኢትዮጵያ ኬንያን ጨምሮ ወደ ስድስት አገራት የስንዴ ምርቷን ለመላክ ዝግጅቷን ጨርሳለች። አሁን በተጀመረው ስንዴን ወደ ውጭ የመላክ ሂደት ከኬንያ፣ ጅቡቲ፣ ሶማሊያ፣ ሱዳን፣ ግብፅና ሌሎች አገራት ጋር ቀጣናዊ ትስስርን ለመፍጠር የሚያስችል ነው።

በዚህ ዓመት ከአገር ውስጥ ፍጆታ የሚተርፍ 32 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት እንደሚኖር በመተንበይ፤ የውጭ ምንዛሬን ለማሳደግና ቀጣናዊ ትስስርን ለማጠናከር የስንዴ ኤክስፖርት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የጠቅላይ ሚኒስትሩ የማክሮ ኢኮኖሚ አማካሪና የኤክስፖርት ኮሚቴ አስተባባሪ አቶ ግርማ ብሩ መናገራቸውም ይህንኑ እውነታ ታሳቢ በማድረግ ነው።

**በአገሪቱ ዓምናና ዘንድሮ ስንዴ የተሸፈነው መሬት 2ነጥብ8 ሚሊዮን ሔክታር ነው፤ በበጋ ወቅት ይመረታል ተብሎ የታሰበውን 50 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴን ሳይጨምር ከ108 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል**

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## እያደገ የመጣው የሳይበር ጥቃትን የመመከት አቅም

> **አስተዳደሩ ሊደርሱ የነበሩ ጥቃቶችን በማስቀረት፣ የደረሱ ጥቃቶችን በማስቆም፣ እንዲሁም አደገኛ የደህንነት ስጋት ሊደቅኑ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በመቆጣጠር ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን ማዳን ችሏል። በዚህም በ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት በሳይበር ጥቃት ምክንያት አገሪቱ ላይ ሊደርስ የሚችል አስራ አምስት ቢሊዮን ብር ኪሳራ ማዳን ተችሏል**

ወርቅነሽ ደምሰው

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሳይበር ጥቃት በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መምጣቱን መረጃዎች ያመላክታሉ። የሳይበር ጥቃት ከቴክኖሎጂ ጋር በተገናኘ የሚፈጸም እንደመሆኑ መጠን ዓለም በቴክኖሎጂ እየመጠቀ ባለበት በዚህ ዘመን የሚቃጣውና የሚፈጸመው የሳይበር ጥቃት በዚያው ልክ አደገኛ የሚባል ነው። በአንድ አገር ላይ ሆን ተብሎ የሚፈጸም የሳይበር ጥቃት አገሪቱን ባንዳፍታ ምስቅልቅሏን አውጥቶ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ሊያስከትል ይችላል።

የሳይበር ጥቃት ሆን ተብሎ ያልተፈቀዱ የኮምፒዩተር ሥርዓቶችን፣ መሠረተ-ልማቶች እና ኔትዎርኮች ላይ አጥፊ ሶፍትዌሮችን በመጠቀም በሕገወጥ መንገድ መረጃዎች መበዝበዝ እና አገልግሎት በማስተጓጎል የሚሰነዘር ጥቃት ነው። በማህበራዊ የትስስር ገጾች ላይ ደግሞ ከባህልና ከሥነ ምግባር ውጪ ባፈነገጠ መንገድ ከሚለጠፉ ምስሎች እና መልዕክቶች ጀምሮ የመረጃ መረብ ተገን በማድረግ በተለያዩ ደረጃዎች የሚፈጸሙ የመረጃ ስርቆቶች የሳይበር ጥቃት ማሳያዎች ናቸው።

መረጃዎች እንደሚያመላክቱት የሳይበር ጥቃት በበርካታ አገራት የደረሰ ሲሆን፣ በጥቃቱም እጅግ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል። ለአብነትም በእ.ኤ.አ 2009 ዩክሬን ላይ የተፈጸመው የሳይበር ጥቃት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውሶች አስከትሎ እንደነበር በወቅቱ የወጡ መረጃዎች ያመላክታሉ። በአንጻሩ ደግሞ የተቃጡ ጥቃቶች የታለመላቸውን ግብ ሳይመቱ የከሸፉባቸው በርካታ ሁኔታዎችም አሉ።

ኢትዮጵያም የዚህ ጥቃት ሰለባ እየሆነች ትገኛለች። በአገሪቱ የፋይናንስ፣ የህክምና፣ የሚዲያ እና የትምህርት ተቋማትን ጨምሮ ሌሎች ወሳኝ መሠረተ-ልማቶችን ኢላማ ያደረጉ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች እንደሚደረጉ ከኢንፎርሜሽን መረጃ ደህነንነት አስተዳደር የተገኘው መረጃ ያመላክታል። ጥቃቶቹን በማክሸፍ በኩል በርካታ ተግባሮች መከናወናቸውን መረጃው ጠቁሟል።

በኢትዮጵያ የሳይበር ጥቃትን የመከላከል ኃላፊነት የተሰጠው የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ነው። አስተዳደሩ በ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት የእቅድ አፈጻጸሙን አስመልክቶ በቅርቡ ለጋዜጠኞች ማብራሪያ የሰጡት የአስተዳደሩ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ሶካ እንደተናገሩት፤ ተቋሙ በስድስት ወራት ውስጥ በሳይበር ጥቃት ሊከሰቱ የነበሩ በርካታ ጉዳቶች ማስቀረት ችሏል።

አስተዳደሩ እንደ አገር የሳይበር ጥቃትን ለመከላከል የሚያስችሉ በርካታ ተግባራት እያከናወነ መሆኑን የሚገልጹት አቶ ሰለሞን፤ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ሊደርሱ የነበሩ ጥቃቶችን በማስቀረት፣ የደረሱ ጥቃቶችን በማስቆም፣ እንዲሁም አደገኛ የደህንነት ስጋት ሊደቅኑ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በመቆጣጠር ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን ማስቀረቱን መቻሉን አብራርተዋል።

እንደ አቶ እሳቸው ገለጻ፤ በአገራችን በስድስት ወራት ውስጥ በርካታ የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች የተሰነዘሩ ሲሆን፣ ጥቃቶችንም በማክሸፍ ረገድ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል። ጥቃቶቹ ቢደርሱ ኖሮ በግለሰብ፣ በተቋማት እና በአገር ደረጃ ሊያደርሱ የሚችሉት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ እና ሥነ-ልቦናዊ ክስረት በጣም ከፍተኛ ይሆን ነበር።

በአጠቃላይ አስተዳደሩ ሊደርሱ የነበሩ ጥቃቶችን በማስቀረት፣ የደረሱ ጥቃቶችን በማስቆም፣ እንዲሁም አደገኛ የደህንነት ስጋት ሊደቅኑ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በመቆጣጠር ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን ማዳን ችሏል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፣ በዚህም በ2015 በጀት ዓመት ስድስት ወራት ውስጥ በሳይበር ጥቃት ምክንያት አገሪቱ ላይ ሊደርስ የሚችል አስራ አምስት ቢሊዮን ብር ኪሳራ ማዳን መቻሉንም ነው የገለጹት።

አቶ ሰለሞን በሳይበር ጥቃት ኢላማዎች በአብዛኛው ትኩረታቸውን በባንኮችና ፋይናንስ ተቋማት ላይ ያደረጉ መሆናቸውንም ጠቅሰው፣ የፀጥታ እና ደህንነት ተቋማት፣ የሚዲያ ተቋማት፣ ቁልፍ የመንግስት ተቋማት ፣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ፣የክልል ቢሮዎች እና የህክምና እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጥቃት ዒላማዎች እንደነበሩ አብራርተዋል።

የሳይበር ጥቃት በመከላከል ላይ ሊሠሩ የሚገባቸው ጉዳዮች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው የሚገልጹት አቶ ሰለሞን፤ አስተዳደሩ እንደ አገር የአገሪቱን የዲጂታል ሉአላዊነት ለማረጋገጥ የሚሠራው ሥራ እንደተጠበቀ ሆኖ ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመሆን የሳይበር ምህዳሩን ደህንነት የማረጋገጥ ድርሻውን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ይገልጻሉ።

### የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነት

በ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ስድስት ወራት ውስጥ የተከሰተውን የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነት በተለያዩ ዘርፎች በሚገኙ 64 ተቋማት (27 የመንግሥት እና 37 የግል) ላይ የተጋላጭነት ዳሰሳ ተደርጓል። ዳሰሳው ከተደረገባቸው ከእነዚህ ተቋማት የዌብ፣ የኔትዎርክ መሠረተ ልማት፣ የሞባይል መተግበሪያዎችን ጨምሮ በተለያዩ መሠረተ ልማቶች 340 የሳይበር ደህንነት የተጋላጭነት የአደጋ ደረጃ (Vulnerability risk level) ክፍተት መገኘቱን እና መድፈን መቻሉ ተመላክቷል።

የሳይበር ደህንነት ተጋላጭነት ስጋቱ ከደረጃ አንጻር ሲታይ 97 ከፍተኛ፣ 154 መካከለኛ እና 89 ዝቅተኛ ደረጃ የተመዘገቡ ናቸው። አጠቃላይ በእነዚህ ሲስተሞች ላይ ሥራው ባይሰራ የሚያመጣው ኪሳራ በብዙ ሚሊዮን ብር የሚገመት ነው። አጥቂዎች የተገኙትን ክፍተቶች ቢጠቀሙባቸው ሲስተሞቹ ምስጢራዊነትን፣ ታማኝነትንና ተጠያቂነትን ሊያጡ ይችሉ አንደነበር ተመላክቷል።

### የሳይበር ደህንነት ስጋት

በአገራችን 2ሺ145 የሳይበር ጥቃቶች እና የጥቃት ሙከራዎች እንደተፈፀሙና ከእነዚህ መካከልም 2ሺ049 ምላሽ የተሰጠባቸው እና የተቀሩት በሂደት ላይ እንዳሉ ተጠቅሷል። በዚህም በመንፈቅ ዓመቱ የሳይበር ጥቃት ሙከራን የመመከት አፈፃፀም 91ነጥብ5 ከመቶ ማድረስ መቻሉም ተጠቁሟል።

በእነዚህ ስድስት ወራት ከተከሰቱት የጥቃት ዓይነቶች እና ኢላማዎች በስፋት የተሞከሩት የሳይበር ጥቃት ዓይነቶች መካከል የድረገጽ ጥቃት፤ ማልዌር፤ የመሠረተ ልማት ቅኝት (Scan)፤ የመሠረተ ልማት ማቋረጥ (DDOS)፤ ሰርጎ መግባት ሙከራ እንደየቅደም ተከተላቸው ከፍተኛ የጥቃት ሙከራ የተደረገባቸው ናቸው።

ለአብነት የሳይበር ጥቃት የተሞከረባቸውን ብንመለከት 14 የድረገጽ ጥቃት እና 381 ሙከራዎች የተደረጉ ሲሆን፣ በማልዌር ጥቃት ሁለት የተሳኩ ጥቃቶች እና 545 ሙከራዎች ተደርገዋል። የመሠረተ ልማት ቅኝት (Scan) ስንመለከት የተሳካ ጥቃት ባይኖርም 869 ሙከራዎች ተደርገዋል። መሠረተ ልማት ማቋረጥ (DDOS) እና ሰርጎ የመግባት ሙከራ የተደረገ ሲሆን፣ የተሳካ ጥቃት ባይኖርም እንደየቅደም ተከተላቸው 57 እና 197 የጥቃት ሙከራዎች መደረጋቸው ተገልጧል። የተለያዩ የኢሜል (ፍራውድ-ክፍያ እንዲፈጸም ማድረግ፣ አካውንት መንጠቅ) ሶሻል ሚዲያ (ስም ማጥፋት፣ አካውንት መንጠቅ፣ ገንዘብ መሰብሰብ) በተመለከተ 80 የተሳኩ ጥቃቶች መፈጸማቸውም ተጠቅሷል።

የተሞከሩ ጥቃቶች ቢደርሱ ኖሮ የመሠረተ-ልማቶችን በማቋረጥ፤ ተቋማት የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች ለተወሰኑ ጊዜያት በማስተጓጎል ሥራዎች እንዳይሠሩ በማድረግ፣ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ተጽዕኖ በማሳደር ገቢ የማስተጓጎል፤ የዳታዎች መሰረቅ እና መጥፋት፤ ዳታዎችን በመመስጠር የቤዛ ክፍያ ገንዘብ መጠየቅ፤ የግንኙነት መንገዶችን በመጥለፍ እና የክፍያን መንገድ በመጠቀም ገንዘብን በማጭበርበር እና በመውሰድ ጉዳት ይደርስ እንደነበር ተመላክቷል።

የሳይበር ጥቃቶች ክብደት ሊያደርሱ ይችሉ ከነበረው ጥፋት መጠን ስንመለከት በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ እና መካከለኛ በሚባል ደረጃ ተቀምጠዋል።

### የመረጃ እና መገናኛ ቴክኖሎጂዎች ቁጥጥር

በአገር አቀፍ ደረጃ ከሚደረገው የሳይበር ደህንነት አደጋ የመቀነስ እና በሚገባ የማስተዳደር ሥራዎች መካከል ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ እና የሚወጡ እንዲሁም በተለያየ ምክንያት የሚወገዱ የመረጃ እና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን መቆጣጠር ይገኝበታል። የቁጥጥር ሥራው የሚካሄደው በአገሪቱ መግቢያ እና መውጫ ኬላዎች ላይ እና ድንገተኛ አካላዊ የመስክ ፍተሻዎች በማድረግ ነው። በዚህ መሠረት ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ፈቃድ ከተጠየቀባቸው 2ነጥብ 158 የተለያዩ ዓይነት ቴክኖሎጂዎች 297 የሚሆኑት የደህንነት ስጋት የሚያስከትሉ በመሆናቸው አደገኛ ተብለው የተለዩ ቴክኖሎጂዎች ወደ አገር እንዳይገቡ ተደርገዋል።

### የሳይበር ደህንነት አደጋ/Risk

አገር አቀፍ የሳይበር ደህንነት አደጋ ደረጃን ለማመላከት በተመረጡ የሚዲያ ተቋማት፣ የፀጥታ እና ደህንነት እንዲሁም ቁልፍ መሠረተ ልማት የሚተዳደሩ ተቋማት ላይ ትኩረት በማድረግ የሳይበር ደህንነት ስጋትን እና ተጋላጭነትን በማጣመር መሥራቱን ለማመላከት ተሠርቷል።

እንደ አጠቃላይ የሳይበር ጥቃት የተሰነዘረባቸው አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ይሰጡት የነበረው አገልግሎት እንዳይቋረጥ በማድረግ የቀረው የገንዘብ ኪሳራ፣ የደንበኞች እንግልት፣ የተጋላጭነት ዳሰሳ በማድረግ የተገኙ ክፍተቶችን መሸፈን ተችሏል። ማስቀረት የተቻሉ ጥቃቶችን መረጃ በመመስጠር የቤዛ ክፍያ ገንዘብ የተጠየቀባቸውን ዳታ ሪኮቨር በማድረግ የቀረ ወጪ፣ እና በመሠረተ ልማቶች ላይ ሊደርስ የነበረውን ጥቃት በማስቀረት የታሰበውን ጉዳት በማስቀረት እንዲሁም ጉዳቱ ደርሶ ቢሆን የድህረ ክስተት ምርመራ ወጪ እና መልሶ ግንባታ ወጪ የሚያስቀሩ ሥራዎች ተሠርተዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ምስቅልቅል በመፍጠር በማህበረሰቡ እርስ በርስ እና ከመንግሥት ጋር ያለውን መስተጋብር ለማበላሸት የተደረገ ጥቃት ከሚኖረው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢንቨስትመንት፣ የፀጥታ እና ደህንነት፣ ቁልፍ የመንግሥት ተቋማት የግንኙነት እና የዳታ ልውውጥ መስተጋብር ተአማኒነቱ፣ ምሉዕነቱ እና እንደተጠበቀ ማድረግ ተችሏል። በዳታ ማፈትለክ አልያም መበላሸት ምክንያት ይመጣ የነበረው ጫና እና ተቋማት ላይ በተደረገ የሳይበር ደህንነት አደጋ//Risk ደሰሳ እና የተቀመጡ መፍትሔዎች መተግበር ወይም በመተግበር ላይ መሆን የተቋማቱን የሳይበር ተቋማቱን የሳይበር ደህንነት ቁመና የማሳደግ ሥራ በመሥራቱ መከላከል የተቻሉ የሳይበር ደህንነት ጉዳቶች እና የመሳሰሉት መሆናቸው ከአስተዳደሩ የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

### እንደ መውጫ

ከጊዜ ወደ ጊዜ አሳሳቢ እየሆነ ያለው የሳይበር ጥቃት በማንኛውም የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ተጠቅሞ ሥራውን በሚሠራ ግለሰብ፣ ተቋምና ቡድን ላይ ሊሰነዘር ይችላል። የሳይበር ጥቃት በአብዛኛው ሲስተሞች፣ የኮምፒዩተር ሥርዓቶች እና መጠቀሚያ መሣሪያዎችን ክፍተት በመጠቀም የሚሰነዘር ነው። ጥቃቱ ፈጻሚዎች (መረጃ ጠላፊዎች) የግለሰቦችን ኮምፒዩተር፣ የስልክ፣ የባንክ ካርድ እና ማንኛውንም ኢንተርኔት ላይ ያኖሩትን መረጃ በመበርበር ጥቃት ሊሰነዝሩ የሚችሉበት ሁኔታ መኖሩ ይታወቃል። እንደዚህ ዓይነቱ የሳይበር ጥቃት ሲፈጸም በግለሰብም ሆነ በአገር ደረጃ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። አንድ መረጃው የተጠለፈበት ሰው ላይ የሚደርሰው ጉዳት በጊዜው በግለሰቡ ላይ ከፍተኛ ድንጋጤን የሚፈጥር ሲሆን፤ በአገር ላይ የሚደርሰው ጉዳት ደግሞ አገርን ከባድ ችግር ውስጥ ሊከት የሚችል ጉዳቶችን ያስከትላል።

የሳይበር ጥቃት በኮምፒዩተርና የኮምፒዩተር መሠረተ ልማትን በመጠቀም አገልግሎት በሚሰጡ ተቋማት ላይ የተደቀነው አደጋ ከባድ እንደመሆኑ መጠን ተቋማት ላይ በየጊዜው አያሌ የሳይበር ጥቃቶች የሚቃጡበት ሁኔታዎች ይታያሉ። የሳይበር ጥቃት እንዲህ አሳሳቢ ከሆነ ዘመኑን የሚመጥኑ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ትኩረት ሰጥቶ የመሥራትን አስፈላጊነት ያመላክታል። በሳይበር ዘመን እየፈረጠመ ያለውን የሳይበር ጡንቻ መመከት የሚያስችል ሥራ መሥራት ካልተቻለ የሳይበር ጥቃት በእጅጉ እየጨመረ በርካታ አገርን ሊጎዱ የሚችሉ ጥቃቶች ሊደርሱ እንደሚችሉ የዘርፉ ምሁራንም ምክረ ሃሳባቸውን ይለግሳሉ።

# ወቅታዊ ትንታኔ

## ኢትዮጵያ - ለፓን አፍሪካኒዝም

ክብረአብ በላቸው

ፓን አፍሪካኒዝም መላውን የዓለም ጥቁር ሕዝብ እንደ አንድ አፍሪካዊ ቤተሰብ የሚመለከት አስተሳሰብ ወይም ንቅናቄ ነው። ንቅናቄው በዋነኝነት የቅኝ ግዛት መስፋፋትን ወይም የነጭ የበላይነትን ለመዋጋት እና አፍሪካዊ አንድነትን ለማጠናከር የታለመ ነበር። ፓን አፍሪካኒዝም በፖለቲካ፣ በሥነጽሑፍ፣ በሙዚቃ፣ በባህል እና በመሳሰሉት ዘርፎች የተቃኘ ሰፊ ንቅናቄ ነበር። ይህ ንቅናቄ መሠረቱን በአገረ አውሮፓ እና አሜሪካ ያድርግ እንጂ የንቅናቄው መንፈስ እና ብርታት ኢትዮጵያ ነበረች። በዚህም ኢትዮጵያ በፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ ውስጥ የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ኃይል እና ኩራት ተደርጋ ትወሰዳለች። የዚህ አስተሳሰብ እና እምነት ገፊ ምክንያት ደግሞ ኢትዮጵያ በማንኛውም የቅኝ ገዥ ኃይል ያልተንበረከከች ብቸኛ አፍሪካዊት አገር መሆኗ ነው።

ኢትዮጵያ እና ፓን አፍሪካኒዝም ያላቸውን ትስስር ብሎም በፓን አፍሪካኒዝም ጽንሰ ሐሳብ ዙሪያ ማብራሪያ እንዲሰጡን ካነጋገርናቸው ምሁራን መካከል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ እና ዓለምአቀፍ ግንኙነት መምህር እና ተመራማሪ ዶክተር ደመቀ አጭሶ ናቸው። እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ ፓን አፍሪካኒዝም በዋናነት ግቡ አንድ እና አንድ ነው፤ ይኸውም የአፍሪካን ውህደት ማምጣት ነው። ውህደት ስንል የመንፈስ፣ የሥነልቦና፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ ውህደት ማምጣት እና በጋራ እንደ አንድ አህጉር በመቆም በዓለም ላይ አፍሪካ ያላትን ተፅዕኖ ከፍ ማድረግ ነው። በተጨማሪም በግሎባል ፖለቲካል ኢኮኖሚ ላይ ያላትን ሚና ማላቅ ነው። በቴክኖሎጂ፣ በንግድ ትስስር አፍሪካ እርስ በእርስ ያለው ውህደት ፀንቶ ሌሎች አገራት የደረሱበት ደረጃም ማድረስ ነው። አፍሪካ አሁንም በ21ኛው ክፍለ ዘመን በርካታ የጥይት ድምጽ የሚሰማባት አህጉር ናት፤ እነዚህን ሁሉ ችግሮች ለመቅረፍ በርካታ ግቦችን ይዞ የሚንቀሳቀስ ነው፤ ዋናው ነገር ግን አፍሪካ በዓለም ላይ ጫና የመፍጠር ብሎም የመደራደር አቅሟን ከፍ እንዲል ግብ ይዞ የሚንቀሳቀስ ታላቅ ርዕይ እና ዓላማ ያለው ነው።

ዶክተር ደመቀ ለዚህ ራዕይ አለመሳካት ተግዳሮት ነው የሚሉትን ሲያነሱ እንዳብራሩት፤ አንደኛ እንደ አህጉር ያሉት በርካታ አገራት ናቸው። የሕዝብ ቁጥሩም አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ይደርሳል ተብሎ ይገመታል፤ እነዚህን ሁሉ አገራት አንድ ላይ ማምጣት በራሱ ፈተና ነው። ሁለተኛ በቅኝ ግዛቱ ምክንያት የቅኝ ገዢዎቻቸው ባህል እና ተጽእኖ የተቋማት ግንባታ ሒደቱ ላይ ጫና አሳድሮባቸዋል። ይህንን ሁሉ ክፍፍል አንድ ላይ አምጥቶ የሚፈለገውን ርቀት ለመሄድ አሁንም የሥነልቦና ዝግጅት ያስፈልጋል። ሦስተኛው ኢኮኖሚ ነው፤ የአፍሪካ ውህደት በዓለም ላይ ያለው የተደማጭነት ሥነልቦና ከፍ እንዲል ማድረግ የተግባር እንቅስቃሴ ይፈልጋል። በተግባር ካልሆነ እውን ሊሆን አይችልም። ለዚህ ደግሞ የኢኮኖሚ አቅም ያስፈልጋል፤ ከውጭ እርዳታ ጥገኝነት መላቀቅ የግድ ይላል። ስለዚህ እነዚህን መሠረታዊ ችግሮች መቅረፍ እና የአፍሪካን ትስስር የፓን አፍሪካኒዝም መንፈስ ማምጣት እንደመናገር ቀላል አይደለም። በመሆኑም ሒደት እና ጽናት ይፈልጋል።

የፓን አፍሪካኒዝም ንቅናቄ ምክንያት ከሆነው አንዱ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አፍሪካውያን በዓለም ኢኮኖሚ ላይ በደንብ የተዋሃዱ ስላልሆኑ እና በተለይ በቴክኖሎጂ ወደ ኋላ በመቅረት እንዲሁም ከሰው ኃይል አኳያ በባርነት ሥርዓት ብዙ ቦታ ተበትነው በመኖራቸው እንደሆነ ተመራማሪው ዶክተር ደመቀ ይናገራሉ። በመጀመሪያ አፍሪካውያኑ በሄዱበት ቦታ ሁሉ እንደ ሰው ሰብዓዊነታቸው ተጠብቆ ከሌላው ዓለም ጋር በደንብ የተዋሃዱ ሆነው ሌላው የሰው ልጅ የሚያገኘውን ክብር አያገኙም ነበር ይላሉ።

አፍሪካውያን በአስተሳሰብም በሌላም በሚሠሩት ሥራ ከሌላው በተለየ አፍሪካዊ በመሆናቸው ብቻ መድልዎ ይፈፀምባቸው ነበር። ስለሆነም ፓን አፍሪካኒዝም በበርካታ የአፍሪካ ምሁራን በዓለም ዙሪያ በተለይ በአውሮፓ እና አሜሪካ የተጠነሰሰ እንቅስቃሴ መሆኑን ዶክተር ደመቀ ያስረዳሉ። በዚህ በፓን የአፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ አፍሪካውያን ይህንን መገለል ለማስቀረት ባሉበት ቦታ ሁሉ የመንፈስ እና የተግባር አንድነትን አምጥተው መቆም እንዳለባቸው እና በዚሁ መንፈስ ሲቆሙ ደግሞ እንደ አንድ አህጉር ብሎም አንድ ድምፅ ተደማጭነታቸውን ለመጨመር እንደሆነም ይናገራሉ። በዓለም ፖለቲካል ኢኮኖሚ ላይ ያላቸው ተጽዕኖ ከፍ እንዲል በአንድነት



ዶክተር ደመቀ አጭሶ



ዶክተር እንዳለው ፉፋ

የመቆም እንቅስቃሴ እንደነበርም ነው ታሪካዊ ዳራውን አውስተው የሚያብራሩት።

እንደ ተመራማሪው ዶክተር ደመቀ አባባል፤ ይህ እንቅስቃሴ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ እና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢ ጠንከር ብሎ ቀጥሏል፤ ከዚያ በኋላ እንቅስቃሴው እያደገ እና እየሰፋ መጥቶ ወደ 1960ዎቹ በቅኝ ግዛት ተገዝተው የነበሩ አገራት ከቅኝ ግዛት እራሳቸውን ማላቀቅ የጀመሩበት ጊዜ ነበር።

በአፍሪካ ብቸኛዋ በቅኝ ያልተገዛች አገር ኢትዮጵያ ናት ያሉት ዶክተሩ፣ ሌሎቹ በቅኝ ግዛት ውስጥ ማለፋቸውን ተናግረዋል። እስቴቶቹም አገራቱም የተመሠረቱት ከቅኝ ግዛት ጋር ተያይዞ ስለነበር በኢትዮጵያ ዙሪያ ያሉ አገራትም የቅኝ ግዛት ውጤት እንደሆኑ ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ ከጎረቤት አገራት ጋር ያላትን ጉዳይ ስታካሂድ የቆየችው ከጎረቤቶቿ ጋር ሳይሆን እነርሱን በቅኝ ከገዙ የቅኝ ገዥዎቻቸው ጋር እንደነበር አውስተዋል። ስለዚህ በ1960ዎቹ አፍሪካን መልሶ ነፃ ማውጣት የሚሉ እንቅስቃሴዎች ብሎም የነፃነት ትግሎች በየቦታው ነበሩ ሲሉ አስረድተዋል።

ዶክተር ደመቀ፣ ኢትዮጵያ ተምሳሌት የሆነችበትን ምክንያት ሲያብራሩ፤ ኢትዮጵያን ለመውረር ከፈረንሳይ፣ ከእንግሊዝ እንዲሁም ከጣሊያን በኩል ፍላጎት ነበር። አገራቱ ኢትዮጵያን በመውረር እንደ ሌሎቹ የአፍሪካ አገራት እናንበረክካታለን የሚል እሳቤ ነበር፤ በሰዓቱ የነበሩ መሪዎች በተለይ ምኒልክ የነበራቸው ቁመና ከአውሮፓውያን ጋር እኩል ባይሆንም ዘመናዊ ዲፕሎማሲ የገባቸው ስለነበር ኢትዮጵያን በዙሪያዋ የከበቡ ኃይላት እርስ በእርስ እንዲጠባበቁ በማድረግ የኢትዮጵያ ሉአላዊነት እንዳይደፈር በማድረግ ትልቅ የዲፕሎማሲ ሥራ መሥራት ችለዋል። በዚህም ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት እንዳትገዛ ማድረግ በመቻላቸው ታላቅ ድል አስመዝግበዋል። የኢትዮጵያ የፓን አፍሪካኒዝም አስተዋፅኦ የጀመረውም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሲሆን፣ በአድዋ ድል ምክንያት ኢትዮጵያ የአፍሪካ የነፃነት ቀንዲል ተደርጋ የምትወሰድ አገር መሆን ችላለች። ድሉ በመሪ ደረጃ ብቻ የተገኘ ሳይሆን እንደ አገርም እንደ ሕዝብም ለአፍሪካ ያበረከትነው አስተዋፅኦ ጉልህ መሆኑንም የሚያሳይ ነው። ይህ ደግሞ ዓለም ያወቀው ሃቅ መሆኑ አይካድም።

ያንኑ ይዞ በ1960ዎቹ ላይ ብዙ የአፍሪካ አገራት ነፃ በወጡበት ወቅት ኢትዮጵያ ስትሠራ የነበረው ‹‹አፍሪካ በአንድነት መቆም አለባት›› በሚል እሳቤ ነበር። ብዙዎች የአፍሪካ አገራት ከቅኝ ግዛቱ በኋላ የተከፋፈለ መንፈስ ነበራቸው፤ ከዚህም የተነሳ የአፍሪካን አንድነት እውን እንዲሆን ለማድረግ ከመግባባት ላይ መድረስ አልቻሉም። በመሆኑም በወቅቱ የነበሩት የኢትዮጵያ መሪ አጼ ኃይለሥላሴ በቅኝ እንዳልተገዛ አገር ለአፍሪካውያን ተምሳሌት በመሆን እርስ በእርስ እንዲግባቡ በማድረግ በ1963 ዓ.ም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በአዲስ አበባ እንዲቋቋም በማድረግ ኢትዮጵያ ለፓን አፍሪካኒዝም መሠረት መጣሏን ዶክተር ደመቀ አስረድተዋል።

እንደ ዶክተር ደመቀ ገለጻ፤ የደርግ ሥርዓትም ለፓን አፍሪካኒዝም በርካታ ሥራዎችን ሠርቷል፤ ቅኝ ግዛቱ ስላለቀ በ1970ዎቹ የተለያዩ አፍሪካውያንን በማሰልጠን ነፃነታቸውን ማግኘት እንዲችሉ የተጫዋተው ሚና ትልቅ ነው። ይህ አካሄድ ቀጥሎ በዘመነ ኢህአዴግ የወቅቱ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ የአፍሪካ ኅብረት መቀመጫ ከአዲስ አበባ ለማንሳት እንቅስቃሴ በነበረበት ወቅት ለኅብረቱ ኢትዮጵያ ያበረከተችውን አስተዋፅኦ በማውሳት የኅብረቱ መቀመጫ ኢትዮጵያ ሆና እንድቀጥል አድርገዋል።

በአሁኑ ወቅት ያሉትም የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ለፓን አፍሪካኒዝም መነቃቃት የራሳቸውን ሚና እየተወጡ ነው፤ በተለይ በጎራቤት አገራት የሰላም ሂደት፣ በአረንጓዴ አሻራ፣ በተባበሩት መንግሥታት አፍሪካ ተገቢውን ቦታ እንድታገኝ፣ ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔ እንዲኖር በማድረግ እየሠሩት ያለው ሥራ የኢትዮጵያ የአፍሪካ ተምሳሌትነት ዛሬም እንዲቀጥል ያስቻለ እንደሆነ ዶክተር ደመቀ ገልፀዋል።

በአርሲ ዩኒቨርሲቲ የሥርዓተ ትምህርት እና ፖሊሲ ጥናት መምህር እና ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር እንዳለው ፉፋ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያን በየጊዜው የመሩ መሪዎች በአገራቸው ዴሞክራሲ በማስረፅ ሂደት ብዙም የተሳካላቸው ባይሆንም ለአፍሪካ አንድነት እና ለፓን አፍሪካኒዝም መርህ የነበራቸው ቁርጠኝነት ትልቅ እንደነበር አስታውሰዋል። በሌላ ጎኑ የአገራት ሥርዓት እና መሪዎች በየጊዜው መቀያየር እና ከዜሮ የመጀመር ዝንባሌ መብዛቱ ብሎም ግጭት መበራከቱ የፓን አፍሪካኒዝሙን እንቅስቃሴ በሰከነ መልኩ ሄዶ ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎታል ይላሉ። አፍሪካውያን የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በውስጥ ተነጋግሮ የመፍታት ባህል አናሳ መሆን ለውጭ ኃይላት ጣልቃ ገብነት ዳርጓቸዋል። በጥናት ላይ የተደገፈ ተቋማዊ ሥራ አለመሠራቱ እና በሁሉም ዘርፍ ችግሮችን በጋራ የመቋቋም ሁኔታ በማህበራዊ ብሎም በኢኮኖሚያዊ ጉዳይ የጋራ አተያይ የመፍጠር ችግር አለባቸው። የውስጥን አካሄድ፣ የመበልፀግ እንዲሁም እርስ በእርስ በጋራ የመሥራት ልምዱ ገና ጥሬ ነው። ሁሉም በሩን ዘግቶ ይቀመጣል፤ ለፓን አፍሪካኒዝሙ ስኬት በጋራ የመሥራት ቁርጠኝነት አሁንም አነስተኛ ነው ብለዋል።

ስለዚህ በተለያዩ ቀጣናዎች በአንድ አንድ አገራት መካከል ያለው ጅምር በመሠረተ ልማት የመተሳሰር እንቅስቃሴ መስፋት በመንገድ፣ በንግድ እንዲሁም ሕዝብ ለሕዝብ ያለውን ግንኙነት እንዲዳብር ማድረግ ይገባል፤ ይህ እንዳይሆን ደግሞ በየጊዜው ሥርዓት እና መንግሥታት በተለዋወጡ ቁጥር እርስ በእርስ ያለው ግንኙነት የሰከነ አለመሆን ተግባራዊነቱ ላይ የራሱን አሉታዊ አስተዋፅኦ አበርክቷል ይላሉ። በየአገራቱ ከሥርዓት ለውጥ በኋላ ያለፈውን ሥርዓት በመውቀስ ብቻ መጠመድ እንዲሁም ጉድለቶችን በማረም መልካም ነገሮችን ማስቀጠል አለመቻል ሌላው ችግር እንደሆነም ዶክተር እንዳለው አስረድተዋል።

ዶክተር ደመቀ፣ ለፓን አፍሪካኒዝሙ ስኬት

**የአገራት ሥርዓት እና መሪዎች በየጊዜው መቀያየር እና ከዜሮ የመጀመር ዝንባሌ መብዛቱ ብሎም ግጭት መበራከቱ የፓን አፍሪካኒዝሙን እንቅስቃሴ በሰከነ መልኩ ሄዶ ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎታል**

የአህጉሪቱ መሪዎች ሚና የመጀመሪያው የውስጥ የፖለቲካ ሥርዓታቸውን ማዘመን መቻል ነው። ሥርዓቱ ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን ማድረግና የሕግ የበላይነት የሰፈነበት የፖለቲካ ሥርዓት መገንባት ወሳኝ ነው። የኢኮኖሚ አቅማቸውን ማሳደግ፣ የዴሞክራሲ ተቋማትን በደንብ ማዘመን እና መገንባት በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ስለዚህ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ለውጦች በውስጥ የፖለቲካ ሥርዓት ላይ መምጣት መቻል አለባቸው። ሁለተኛው አፍሪካ የጥሬ ዕቃ አቅራቢ ብቻ ሆና መቀጠል የለባትም። ርካሽ የጥሬ ዕቃ እና የሰው ኃይል እየፈሰሰ ያለው ከአፍሪካ አህጉር ወደ ሌሎች አህጉራት ነው። ደሴት ሆኖ መኖር ስለማይቻል ከዓለም ጋር ትስስር መፍጠር ጥሩ ነው። ነገር ግን ጥቅም እና ጉዳቱን ማስላት አስፈላጊ ነው።

ዶክተር ደመቀ እንደሚሉት፤ ጥሬ ዕቃ ወደ ውጭ ከመላክ ይልቅ እሴት ጨምሮ መሸጥ የሚቻልበትን የአሠራር ዘዴ መፍጠር፣ የቴክኖሎጂ አቅምን ማዳበር እና የአፍሪካ አገራት ከሌላው ዓለም ጋር እንዲኖራቸው የሚፈልጉትን ያህል ግንኙነት እርስ በእርስ በተለይ የንግድ ትስስር እንዲኖራቸው በርትተው መሥራት አለባቸው። ሌላው የአፍሪካ መሪዎች በየጊዜው ግንኙነት በማድረግ ተቋማት እየተገነቡ ነው ወይ? የሚለውን በመገምገም ሌሎች የደረሱበት የውህደት ደረጃ በአፍሪካ ውስጥም እንዲመጣ በተለይ ነፃ የንግድ ቀጣና ለማስፋፋት ቁርጠኝነት በመውሰድ መሥራት ያስፈልጋል። አህጉሪቱ ዛሬም በእርዳታ ሰጪ አገራት የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ውስጥ እንዳትወድቅ በፋይናንስ እራስን ለመቻል በትጋት መስራት የግድ ይላል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# በከተማም በገጠርም ለሴቶች ችግር የሆነው የውሃ አቅርቦት

**ሰላማዊት ውቤ**



ወይዘሮ እንግዳ ካሳ ስድስት ኪሎ በአካባቢ መኖር ከጀመሩ አራት ዓመታቸው መሆኑን ይናገራሉ፡፡ በእነዚህ አራት ዓመታት ወስጥ ሁለቱን ዓመት ውሃ ሙሉ ቀን ሳይቆራረጥ ያገኙም እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡ ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ግን ውሃ ከመቆራረጡም በላይ ሳይመጣ ሳምንታት ይቆጠራሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ደግሞ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኪሳራዎች መዳረጋቸውን ያብራራሉ፡፡

ውሃ መጣች ብለው ስራ መስራት ሲጀምሩ ወዲያው ትቋረጣለች፡፡ ከዚህ በኋላ ትመጣለች ተብሎ 10 እና 15 ቀን ሲጠበቅ ማሽን ውስጥ ሊታጠብ የገባው ልብስ ሳይቀር ይበላሻል፡፡ ይህ ከሚሆን እያሉ አሁን አሁን ውሃ እያስገዙ ማሳጠብ ጀምረዋል፡፡

ውሃን ትመጣ ይሆናል በሚል ተስፋ በቤት ውስጠ የሚጠራቀመውን ልብስ በእሳቸው ጉልበት የሚታጠብ አለመሆኑን የምትናገረው ልጃቸው ችግሩ በጣም የከፋ በመሆኑ እሷም ሥራ ለብሳ የምትሄደው ልብስ እስከማጣት የምትደርስበት ጊዜ መኖሩን ትናገራለች፡፡ እኛም ባገኘናት ጊዜ በቤት ውስጥ የተከማቸውን ልብስ ለማጠብ ከስራ ቀርታ ውሃ ከሩቅ መንደር እያስገዛች በማጠብ ከላይ ነበረች፡፡ የወይዘሮ እንግዳ ልጅ አክላም ልብስን በዚህ መልክ አጠብን ነገር ግን የግል ንጽህናችንንስ እንዴት እንጠብቅ የት ሄደን ገላችንን እንታጠብ ስትልም ትጠይቃለች፡፡

እዛው ስድስት ኪሎ አካባባቢ የሚኖሩት ሌላዋ ወይዘሮ ውብዓለም ደምሴ ይባላሉ እሳቸውም በውሃ እጦት እየተሰቃዩ ካሉት የአካባቢው ነዋሪዎች አንዷ ናቸው፡፡ እሳቸው እንደሚሉትም ነዋሪው አብዛኛው ጡረተኛ ነው ፤ የመንግስት ሠራተኛም የሆነና በልጆቹም እየተረዳ የሚኖር አለ፡፡ እያንዳንዱ ቤት ውስጥ ቢያንስ ስድስት ቢበዛ እስከ 15 ልጆችና ቤተሰብ ይኖራሉ ፡፡ አሁን ላይ ኑሮ እየከበደ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በየቤቱ ቤተሰብ ማስተዳደር የልጆች ትምህርት ቤት ክፍያ ቀለብ ትራንስፖርት በጠቅላላው ብዙ ወጪዎች አሉ ፤ በእነዚህ ላይ የውሃ ወጪ ሲጨመር በእጅጉ እንደሚያማርርም ያብራራሉ፡፡

"እኔ ሥራ የለኝም፡፡ ወጪዎቻችንን በሙሉ የሚሸፍነው ባለቤቴ ነው፡፡ ባለ 20 ሊትር ጀሪካን ውሃ በ25 ብር እንገዛለን ፤ ለዚህ የሚሆን ገንዘብ ደግሞ ባለቤቴን በየቀኑ መጠየቅ ያሰለቻል ፡፡ እኛ በባሎቻችን ሥር ነው የምንተዳደረው፡፡ ባሎቻችን ሴቶች ለብዙ ነገር ውሃ እንደሚያስፈልገን ግንዛቤ ስለሌላቸው ደጋግሞ ገንዘብ መጠየቁ አያሳቀቀን ነው" ብለዋል፡፡ አራት ህፃናት ልጆች እንዳላቸው የሚናገሩት ወይዘሮዋ በተለይ ሦስቱ ትምህርት ቤት የገቡ በመሆናቸው ዩኒፎርማቸውን ለማጠብ ውሃ በየጊዜው ቢያስፈልግም ባለመገኘቱ የቆሸሸ ለብሰው ለመሄድ ተገደዋል፡፡ እንዳንዴም ለእጅ መታጠቢያ የሚሆን ውሃ እያጣን እጃቸውን ሳይታጠቡ የሚበሉበትም ጊዜ መኖሩን ይናገራሉ፡፡

በሰፈሩ ካለው ነዋሪ በተለይ የሴቶች ፤ ከሴቶችም የደረሱ ልጃገረዶች ይበዛሉ የሚሉት ወይዘሮ ውብዓለም ለነዚህ ልጃገረዶቹ ንጽሕና መጠበቂያ ውሃ ያስፈልጋል፡፡ እኔም በቅርቡ የወለድኩ አራስ በመሆኔ ለእኔና ለህጻኑ ልጄ ጽዳት መጠበቂያ ውሃ የግድ ነው፡፡ ነገር ግን ውሃ የለችም፡፡ ውሃ ገዝቶ ሁሉን ለማድረግ ደግሞ ወጪው ኢኮኖሚን የሚፈታተን እየሆነ መጥቷል ይላሉ፡፡

በሌላ በኩልም ሌሊት እየተነሱ ውሃ የሚቀዱት ነዋሪዎች የጀርባ አጥንትና ሌላ የአጥንት ህመም ያላቸው ፤ የእግርና እጅ እንዲሁም የአስም ህመም ታማሚዎች ናቸው፡፡ ከሌሊቱ ስምንት፤ ዘጠኝና 10 ሰዓት ውሃ መጣች ፤አልመጣች በሚል ቁጭ ብለው ያድራሉ? ቀን ሳይተኛ ሌሊት ሳይተኛ እንዴት ይቻላል? መንግሥት ቢሮዎቹን መፈተሽ አለበት፡፡ የውሃ አቅርቦት የሙስና ጉዳይ ሊሆን ይችላልና ሲሉም ወይዘሮ ውብዓለም አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ወይዘሮ አፀደ ዓለሙም የዛው አካባቢ ነዋሪ ሲሆኑ እንደሚናገሩትም በአካባቢው ከ50 ዓመት በላይ ኖረዋል፡፡ የመንግሥት ሠራተኛ በመሆናቸው ሌሊት እየተነሱ ውሃ መቅዳቱ በሥራ ገበታቸው ላይ ጭምር ጫና እየፈጠረባቸው ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ መጣች አልመጣች እያሉ ሌሊት የምትመጣዋን ውሃ በመጠባበቅ ነው የእንቅልፍ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት፡፡ እንደዚህም ተጠባብቀው ሳትመጣ የምትቀርበትና መጥታም የተደቀነው ባሊ ግማሽ ሳይደርስ የምትቋረጥበት ጊዜ ብዙ ነው፡፡

እያንዳንዱ ቤተሰብ በሥሩ ስምንትና 10 ሰው አለው ዘጠኝ ቤተሰብ ያለው ሊጥ አቡክቶና እንጀራ ጋግሮ፤ ወጥ ሰርቶ፤ ልብስ አጥቦና ጽዳቱን ጠብቆ ማስተዳደር ስለማይቻልም ማልደው ውሃ ፍለጋ መቅጃዎቻቸውን በማሰባሰብ ከሰፈር ውስጥ መኪና ያላቸውን ለምነው ከቤላና ምኒሊክ ሆስፒታል አካባቢ ሊቀዱ ይሄዳሉ፡፡ አንዳንዴ ታዲያ ረፍዶባቸው ከሥራ የሚቀሩበት ጊዜ አለ፡፡ ቢሄዱም ሌሊት እንቅልፍ አጥተው ስለሚያድሩ ሥራ በአግባቡ ሳይሰሩ ሲያንቀላፉ ውለው ነው የሚመለሱት፡፡

አቶ ጌታቸው በሪሁን እንደሰጡን አስተያየት በተለይ ሴቶች በውሃ እጦት እየተቸገሩ ነው ፤ የሚመለከተው አካል ስለችግሩ ሲጠየቅ የሚሰጠው ምላሽ ውሃው ከቁልቁለት ወደ ዳገት አይወጣም ነው፡፡ ሆኖም ድሮም ያለነው መድኃኒዓለምና ውሃ ክፍል ፊት ለፊት ዳገት ላይ ነው ፡፡ ቀድሞ 24 ሰዓት ሳምንቱን ሙሉ ውሃ ይኖረን የነበረው በዚሁ ዳገት ተቀምጠን ነው ፡፡ ያኔ ዳገቱ ለምን አልከለከለም ሲሉም ይጠይቃሉ፡፡ በመሆኑም ነዋሪዎች መስመሩ ተለውጧል ወይም የሙስና ሥራ እየተሰራበት ነው እስከማለት ደርሰዋል፡፡ ውሃ የሚሸጡ ሰዎች እንደ እነሱ ሁሉ ዳገት ላይ መኖራቸውንና 24 ሰዓት ውሃ የሚያገኙበት የነበረ መሆኑንም ይገልፃሉ፡፡ ውሃ ከሱቅ ለሚያመላልሱላቸው ሰዎች 25 ብር ይከፍላሉ፡፡ ልብስ ሲታጠብ በትንሹ 10 ጀሪካን ስለሚገዙ 250 ብር ያወጣሉ። ሆኖም እነሱ ጀሪካን ስለሌላቸውና የሱቁ ጀሪካን ስለማይታጠብ ውሃው ዘይቱ የሚንሳፈፍ በመሆኑ ንጹህና ለምግብ መስርያ የሚያገለግል አይደለም፡፡

"ይሄም ብቻ ሳይሆን አምስት ዓመት አልጋ ላይ የተኛች ልጅ አለችኝ" የሚሉት የአካባቢው ነዋሪ አቶ መንግሥቴ ላቀው ይህች ልጅ ወጣት እንደመሆኗ የወር አበባ ንጽህና መጠበቂያን መቀየር ብቻ ሳይሆን መንቀሳቀስ ባለመቻሏ ሁሉን ነገር መኝታዋ ላይ ሆና ነው የምትገለገለው፡፡ ለዚህ አገልግሎት ታዲያ በየቀኑ ብቻም ሳይሆን 24 ሰዓት እርዳታ ትፈልጋለች ፤ሌሊት ውሃ ለመቅዳት ደግሞ እጠብቃለሁ" ሲሉ በምሬት ይህ ችግር ግን የተፈጠረው በአሰራር ዝንፈት ነው ይላሉ፡፡

የሎዛን ሁቴል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት ሥራ አስኪያጅ አቶ ሳሙኤል በቀለ ወደ ድርጅቱ ከመጡ ሦስት ዓመታቸው ሲሆን ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ግን በውሃ እጥረት ምክንያት ድርጅታቸው ሥራ ለመሥራት በእጅጉ ሲቸገር መቆየቱን ይናገራሉ፡፡ ይሄንኑም ምስካይ ሕዙናን መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን አጠገብ ለሚገኘው ውሃ ልማት አሳውቀዋል፡፡ ፈጣን ምላሽ ባለማግኘታቸውም ችግሩ በተለይ በሴት ነዋሪዎች

**እያንዳንዱ ቤት ውስጥ ቢያንስ ስድስት ቢበዛ እስከ 15 ልጆችና ቤተሰብ ይኖራሉ ፡፡ አሁን ላይ ኑሮ እየከበደ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በየቤቱ ቤተሰብ ማስተዳደር የልጆች ትምህርት ቤት ክፍያ ቀለብ ትራንስፖርት በጠቅላላው ብዙ ወጪዎች አሉ**

ላይ ከባድ ጫና እየፈጠረ መሆኑን ከሚገልጽ ማሳሳቢያ ጋር የነዋሪውን ፊርማ አሰባስበው አስገብተዋል፡፡ ሁሌም መልሳቸው መስመሩ ወደ ላይ ወደ ዳገት አይወጣምና ፤ እጥረት አለ እንጂ ይመጣል ነው፡፡

ድርጅቱ በየዓመቱ ከ 100 ሺህ ብር በላይ ለመንግሥት ግብር የሚከፍልና ከስምንት ድርጅቶች በላይ ቢያስተዳድርም የነዚህን ወጪዎች መሸፈን አልቻለም፡፡ ሆቴሉ 17 አልጋ ያለው መሆኑን የጠቀሱት አቶ ሳሙኤል ውሃ ለአንሶላ ማጠቢያ ፤ ለሻወር ፤ለቤት ጽዳትና ለብዙ ነገሮች እንደሚያስፈልጋቸው ያነሳሉ፡፡ በየአራት ቀኑ በቦቴ ለማስገልበጥ ሦስት ሺህ ብር እንደሚከፍሉም ነግረውናል፡፡

ይሄን የነዋሪዎቹን ቅሬታ ይዘን ፊት ለፊታቸው ወደሚገኘው የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን የጉለሌ ቅርንጫፍ ጎራ አልን፡፡ የቅርንጫፉ ስራ አስኪያጅ አቶ አምባዬ አሰፋ እንደሚሉት ፤ " የውሃ ችግር አለብን" ነዋሪዎቹ ከዚህ በፊት ወደ እሳቸው መጥተው ቅሬታቸውን አላቀረቡላቸውም፡፡

የሕብረተሰቡ ቅሬታም ሆነ አራዳን ጨምሮ ለሦስት ክፍለ ከተማ የውሃ ስርጭት መስጠቱን አስታውሰው የሕብረተሰቡ ቅሬታ የቀረበበት ጉለሌ ክፍለ ከተማ ላይ ውሃን የተመለከተ ሪፖርት ከዚህ ቀደም እንዳልደረሳቸው ተናግረው ቅርንጫፍ አቀማመጥ ጋር በተያያዘ በፈረቃ እየተሰጠ መገኘቱ የሚታወቅ እንጂ አዲስ አለመሆኑን ተናግረዋል፡፡ እያንዳንዱ የውሃ ስርጭት ከኤሌትሪክ ኃይል ጋር የተገናኘ ስለሆነ በተለያዩ ምክንያቶችም የውሃ መቆራረጥ ሊኖር መቻሉንም እውነት ነው ብለዋል፡፡ ፈረቃው በሳምንት አንድ ቀን መሆኑና በዚህ ወቅት መብራት ቢቋረጥ ውሃው ላይደርስ የማይችልበት ሁኔታ ሊፈጠር መቻሉንም ጠቅሰዋል፡፡ የነዋሪዎችን ቅሬታ የተመለከተ ሪፖርትም ደርሷቸው እንደማይውቅ ተናግረዋል፡፡

ሥራ አስኪያጁ እንደሚናገሩት የነዋሪዎቹ መስመር ነባር ነው፡፡ ሆኖም በባለሥልጣኑ በኩል ይሄን መስመር ለመዘጋትም ሆነ ለመክፈት የተካሄደ ሥራ የለም፡፡ ነገር ግን ችግሩ በተጨባጭ አለ የሚባል ከሆነ ቅርባችን በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ወርዶ ማየት ስለሚገባን ወርደን አይተን እናስተካክላለን» ብለዋል፡፡

ሥራ አስኪያጁ ቅርንጫፉ የካና አራዳን ጨምሮ ለሦስት ክፍለ ከተማ የውሃ ስርጭት ይሰጣል፡፡ የሕብረተሰቡ ቅሬታ የቀረበበት ጉለሌ ጉለሌ ክፍለ ከተማ ላይ ከአካባቢው መሬት አቀማመጥ ጋር በተያያዘ ውሃ በፈረቃ እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ይሄ ውሃ በፈረቃ የሚሰጥበት ፕሮግራም እንደ አገር እየተሰራበት የሚገኝ እንጂ አዲስ አይደለም፡፡ እያንዳንዱ የውሃ ስርጭት ከኤሌትሪክ ኃይል ጋር የተገናኘ ስለሆነ በተለያዩ ምክንያቶችም የውሃ መቆራረጥ ሊኖር የመቻሉንም ዕውነት ሥራ አስኪያጁ አምነዋል፡፡ ፈረቃው በሳምንት አንድ ቀን መሆኑና በዚህ ወቅት መብራት ቢቋረጥ ውሃው ሊደርስ ማይችልበት ሁኔታ ሊፈጠር መቻሉንም አውስተዋል፡፡

ችግሩ መኖሩን ነዋሪዎች ነግረውናል፡፡ ይሄም ችግሩ ለመኖሩ አንድ ማረጋገጫ ሲሆን ጉዳዩ የሚመለከታቸው የዚሁ ቅርንጫፍ አንድ የሥራ ሂደት ኃላፊ ነዋሪዎቹ ያቀረቡትን ቅሬታ ቀደም ብለው ሰምተው የነበረ መሆኑን ነግረውናል፡፡ በመሆኑም በተለይ ሴቶች ውሃ ለመቅዳት ሩቅ ቦታ ከመሄድ ጀምሮ በይበልጥ ተጎጂ የሆኑበትን የውሃ ችግር ወርዶ በማየት መፍታቱ አግባብ ነው በማለት ጽሑፋችንን ቋጨን፡፡

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

በታኅሣሥ ወር በ1961 ዓ.ም በታተሙት ጋዜጦች የሚያሳዝኑ ፣ትንግርትንና ጥያቄን የሚያጭሩ እንዲሁም በእኛ አገር የተከሰተ ነው የሚያስብሉ ዘገባዎች ለንባብ በቅተዋል። እኛም በዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ አምዳችን እነዚህን ዘገባዎች ለትውስታ ያህል መርጠናል። በተጨማሪም ከልማት ጋር የተያያዙ ዘገባዎችን አካተናል። አማኑኤል ሆስፒታል ለታማሚዎች የሲኒማ አዳራሽ በሕዝብ ትብብር እያሠራ እንደሆነ የሚገልፅ አንድ ዘገባም ዛሬ የሲኒማ አዳራሹ ታሽጎ ነው ወይስ የሚታይ ሲኒማ ጠፍቶ ነው ብለን እንድንጠይቅ ያደርጋል።

**ግመል ሰው በላ**

**መቀሌ ፣(ኢ-ዜ-አ) በእንደርታ ወረዳ ውስጥ** ዓዲ አሙቆ በተባለው ቀበሌ የሚኖሩ ሁለት ሰዎች በግመል ተነክሰው ሆስፒታል የገቡ መሆናቸውን የትግሬ ጠቅላይ ግዛት ፖሊስ ማስታወቂያ ክፍል ገለጠ።በግመል የተነከሱትም ሰዎች ዕቁባ ሐድጎ የተባለ የ፲፫ ዓመት ወጣትና አቶ ነጋሽ ግርማ የተባሉ ሰው ናቸው።

ግመሉ ይህን አደጋ ሊደርስ የቻለው ፣ በመጀመሪያ ዕቁባ ሐድጎን ራሱ ላይ ነክሶ ብዙ አንገላታው። በዚህም ጊዜ አቶ ነጋሽ ግርማ ወደ ግመሉ ተጠግተው የዕቁባይን ሕይወት ለማዳን ሲሞክሩ ፣ርሳቸውንም ከራሳቸውና ከእግራቸው ላይ በመንከስ ከፍ ያለ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል።

ቁስለኞቹ አሁን መቀሌ ከተማ በሚገኘው ከልዑል ራስ ስዩም መንገሻ መታሰቢያ ሆስፒታል ገብተው በሕክምና ላይ ይገኛሉ።

በሰዎቹ ላይ አደጋ ያደረሰው ግመል ግን አቶ ሐረጎት ግርማ በተባሉ ሰው አማካይነት በረሽ ጠብመንጃ የተገደለ መሆኑን የጠቅላይ ግዛቱ ፖሊስ የማስታወቂያ ክፍል በተጨማሪ አስታወቀ። የእንደርታ ወረዳ የሚገኘው በትግሬ ጠቅላይ ግዛት በእንደርታ አውራጃ ግዛት ነው።

**(ታኅሣሥ 2 ቀን 1961 ከወጣው አዲስ ዘመን)**

**ቦምብ ፈንድቶ ሰው ገደለ**

በጨቦና ጉራጌ አውራጃ በበቾ ወረዳ በኢሉ ምክትል ወረዳ ግዛት አንድ ቦምብ ፈንድቶ ሰው ሲገድል ሁለት ሰዎች አቆሰለ።

አደጋው የደረሰው ኅዳር ፳፯ ቀን ፲፩፩ ዓ.ም ዳባ በዳዳ ፣ሁንዴ መስቀሌ የተባሉ ሰዎች እመት ደሴ ጉሜ ቤት ውስጥ አንድ የእጅ ቦምብ ሲፈታቱ ነው። ቦምቡ በፈነዳበት ጊዜ ዳባ በዳዳ የተባለው ወዲያውኑ ሲሞት ፣ሁንዴ መስቀሌና እመት ደሴ ጉሜ የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል ሲሉ ሻለቃ ከፍያለ ወርቁ የጨቦና ጉራጌ አውራጃ ፖሊስ ምክትል አዛዥ ማስታወቃቸውን የሸዋ ጠቅላይ ግዛት ፖሊስ የማስታወቂያ ክፍል ገለጠ።

**(ታኅሣሥ 2 ቀን 1961 ከወጣው አዲስ ዘመን)**

**ብታምኑም ባታምኑም**

**አንድ የ62 ዓመት አዛውንት ቀንድ አበቀሉ**

**ጐንደር ፣(ኢ-ዜ-አ) አንድ የ፷፪ ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሰው ራሳቸው ላይ ቀንድ በቀለ።** በበጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት በጀምናምራ ወረዳ በሳህላ ምክትል ግዛት ነዋሪ የሆኑት አቶ ወልዴ መራ ቀንድ ራሳቸው ላይ የበቀለው ከ፫ ዓመታት በፊት መሆኑን ባለቤቱ መናገራቸውን የደረስጌ ክሊኒክ አላፊ አቶ አያሌው መኰንን ገለጡ።

አቶ ወልዴ መራ ይኸው ከ፫ ዓመት በፊት የበቀለው ቀንድ በየጊዜው እያደገ ወደ ቤት ሲገቡና ሲወጡ ብዙ የሚያስቸግራቸው መሆኑን ለክሊኒኩ አላፊ በሰጡት ቃል አስታውቀዋል።

ከዚህም በቀር እኚሁ ቀንድ የበቀለባቸው አዛውንት ለአንዳንድ ሥራ ወደ ጫካ በሚሔዱበት ጊዜ ግራና ቀኝ እየያዘ የሚያስቸግራቸው መሆኑንም ጨምረው ገልጠዋል።

አቶ ወልዴ መራ ከራሳቸው ላይ የበቀለው ቀንድ አራት ሳንቲ ሜትር ርዝመት ያለው ሲሆን ፣ይኸው ቀንዱ የበቀለበት ሥፍራ ግን በየትናው ወገን እንደሆነ አይገልጥም።

አቶ ወልዴ መራ የሚተዳደሩት በእርሻ ሥራ ሲሆን ፣ትዳርም ያላቸው ሰው ናቸው። ይኸው በአቶ ወልዴ ላይ የደረሰው አስደናቂ ታሪክ በክፍሉ ባላባት በአቶ ቸኮል ንጉሤ ተባባሪነት የተገኘ መሆኑን ወኪላችን ከጐንደር ገልጧል።

**(ታኅሣሥ 5 ቀን 1961 ከወጣው አዲስ ዘመን)**

**ለአማኑኤል ሆስፒታል**

**ሲኒማ ቤት ርዳታ ይሰበሰባል**

የአማኑኤል ሆስፒታል የማኅበራዊ ጉዳይ አገልግሎት ሠራተኞች ፣በቅርቡ ተሠርቶ የነበረው የአእምሮ ሕሙማን የመንፈስ ማደሻ የመደሰቻ (ሲኒማ) አዳራሽ በአገልግሎት ላይ እንዲውል የሥራ ማሚያ ርዳታ በገንዘብ መልክ በሌላም ከልዩ ልዩ በጎ አድራጊዎች ድርጅት ርዳታ እያገኙ ናቸው።

የሲኒማው አዳራሽ ለመሥራት የበቃው፣ የሆስፒታሉ የማኅበራዊ ጉዳይ አገልጋዮችና አንድ የሰላም ጓድ ባልደረባ ከበጎ አድራጊዎች በሰበሰቡት ገንዘብና የአሜሪካ ተራድኦ ባዋጣው ርዳታ ሲሆን ፣ የአዳራሽ ወለል ጣሪያውና የፕሮጀክተሩ ማስቀመጫው ተሟልቶ ስለአላለቀ ፣የማኅበራዊ ጉዳይ አገልግሎት አስተባባሪዎች ርዳታ ከየትም ቢሆን ማግኘት ግድ ሆኖባቸዋል።

አቶ ደበበ በየነ ፣በአማኑኤል ሆስፒታል የማኅበራዊ ጉዳይ አገልግሎት ሠራተኞች እንደገለጡት ጥቂት በጎ አድራጊ ኩባንያዎችና ድርጅቶች የመሣሪያና የገንዘብ አገልግሎት ሲያደርጉልን ከሌሎችም እናገኛለን ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

እስካሁን ለሆስፒታሉ የለገሡት ኩባንያዎችና ስጦታዎች ፣የኢትዮጵያ ሲሚንቶ ኮርፖሬሽን ፩ ሺ ብር፣ የኤካፍኮ ኩባንያ ፪፻፳ ብር የሆነ የጣሪያ ፋየዚቲሲዲ፣ ኩባንያ በግምት ፬፻፪፻፹ የሆነ ፣ ፺፯ ኩብ ሜትር ሸክላ ለወለል ምንጣፍ የሚሆን የሜጋ ቀለም ኩባንያ በ፩፻፳ብር የሚገመት ፲፰ ጋሎን ቀለም ናቸው ።

**(ታኅሣሥ 4 ቀን 1961 ከወጣው አዲስ ዘመን)**

# ዓለም አቀፍ



## የናይጄሪያ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ውጤት በአንዳንድ ግዛቶች ይፋ መደረግ ጀመረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በናይጀሪያ ወታደራዊ አገዛዝ እአአ 1999 ካበቃ በኋላ ከፍተኛ ፉክክር ታይቶበታል የተባለው የምርጫ ውጤት መታወቅ ጀምሯል።

በበርካታ ምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ውጤቶች እየተለጠፉ ሲሆን፤ ከደቡብ ምዕራብ ኤኪቲ ግዛት የወጡ ይፋዊ ውጤቶች የገዢው ፓርቲ እጩ ቦላ ቲኑቡ አሸናፊ መሆናቸውን አሳይተዋል።

በዚህ ምርጫ ሦስት እጩዎች ጠንካራ ተፎካካሪ እንደሚሆኑ ይጠበቃል። ፒተር ኦቢ ከሌበር ፓርቲ፣ ቦላ ቲኑቡ ከገዢው ኦል ፕሮግረሲቭ ኮንግረስ እና አቲኩ አቡበከር ከፒፕልስ ዴሞክራቲክ ኮንግረስ ናይጄሪያን ሊመሩ የሚችሉ ናቸው።

ከሦስቱ ፖለቲከኞች በተጨማሪ ሌሎች 15 ፕሬዚዳንታዊ እጩዎች በዚህ ምርጫ ተሳታፊ ሆነዋል።

አንድ እጩ አሸናፊ ለመሆን አብዛኛውን ድምጽ ማግኘት ወይም ደግሞ በናይጀሪያ 36 ግዛቶች ከተሰጡት ድምጾች በሁለት ሦስተኛ ግዛት ከተሰጠው ድምጽ 25 በመቶ ማግኘት ይኖርበታል።

ይህን ማግኘት የማይችል እጩ ካለ በ21 ቀናት ውስጥ ዳግም ምርጫ ይካሄዳል።

በአፍሪካ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ድምጽ ሰጪ ተሳትፎ በሚያደርግበት በዚህ ምርጫ በተለይ ናይጀሪያውያን ወጣት ድምጽ ሰጪዎች በከፍተኛ ቁጥር ወጥተው መምረጣቸው ተገልጿል።

በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎች ቅዳሜ ዕለት ባጋጠሙ መዘግየቶች እና ጥቃቶች የድምጽ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት እስከ አለፈው እሁድ ድረስ እንዲራዘም ተደርጓል።

በሌሎች ስፍራዎች ደግሞ የድምጽ አሰጣጥ ሊጠናቀቅ ሰዓታት እስከ ቀሩበት ድረስ መራጮች ድምጽ አልሰጡም ነበር።

በመዲናዋ አቡጃ ደግሞ መራጮች ድምጽ ለመስጠት ሰዓታት ለመጠበቅ ተገደዋል። ለመጀመሪያ ጊዜ የምትመርጠው ሱዛን ኤክፖህ ድምጽ ለመስጠት በምርጫ ጣቢያ ለ13 ሰዓታት መጠበቋን ለቢቢሲ ተናግራለች።

ሪቨርስ እና ሌጎስ በተሰኙ ግዛቶች ደግሞ ውጥረት ሰፍኗል። የውጥረቱ ምክንያት ደግሞ ፖለቲከኞች ድምጽ ቆጠራ ላይ መጭበርበር እንዳያጋጥም ደጋፊዎቻቸው ወደ ምርጫ ጣቢያዎች ሄደው ቆጠራውን እንዲከታተሉ መልዕክት ማስተላለፋቸው ነው።

በአስር ሺዎች ከሚቆጠሩ ምርጫ ጣቢያዎች የተሰባሰቡ ውጤቶች እየተደመሩ ነው። የምርጫ ኃላፊዎች የምርጫ ውጤቶችን ይዘው ወደ አቡጃ ካመሩ በኋላ ከመዲናዋ የየግዛቱ አሸናፊዎች ይፋ ይደረጋሉ።

አጠቃላይ የምርጫ ውጤቱ ከጥቂት ቀናት በኋላ ይፋ ይደረጋል ተብሎ ይጠበቃል።

ምርጫውን የሚያሸንፍ እጩ፣ ናይጄሪያ ላይ ለተጋረጡት የኢኮኖሚ ችግር፣ ለወጣቶች ሥራ አጥነት እና ሰፊ የደህንነት እጦች ምላሽ መስጠት ይኖርበታል።



## በጣሊያን ባሕር ዳርቻ በሰጠመችው ጀልባ የሞቱት ስደተኞች ቁጥር ከ100 በላይ ሊሆን ይችላል ተባለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በደቡባዊ ጣሊያን ባሕር ዳርቻ ስደተኞችን አሳፍራ ስትጓዝ በሰጠመችው ጀልባ ምክንያት የሞቱት ሰዎች ቁጥር ከ 100 በላይ ሊሆን እንደሚችል ተሰግቷል።

በደቡባዊ ጣሊያን የባሕር ዳርቻ አቅራቢያ እሁድ ዕለት በደረሰው በዚህ አደጋ በርካታ ሕጻናትን ጨምሮ እስካሁን 62 ሰዎች መሞታቸው ተረጋግጧል።

ካላብሪያ ከተባለችው የባሕር ዳርቻ የመዝናኛ ክልል አቅራቢያ በአደጋው የሞቱ ሰዎች አስከሬን የተገኘ ሲሆን፣ ከሟቾቹ መካከልም አንድ ጨቅላን ጨምሮ 12ቱ ልጆች መሆናቸው ተዘግቧል።

የጣሊያን ባለሥልጣናት በጀልባዋ ተሳፍረው ከነበሩት መካከል የደረሱበት ያልታወቀ በመኖራቸው የሟቾች ቁጥር ከፍ ሊል ይችላል ሲሉ ስጋታቸውን ገልጸዋል።

በጀልባ ተሳፍረው የነበሩ ሰዎች ቁጥር እስካሁን በትክክል አልታወቀም። በጀልባዋ ተሳፍረው የነበሩ እና በሕይወት የተረፉ ስደተኞች ግን ጀልባዋ ላይ 150 ሰዎች ተሳፍረው ነበር ብለዋል።

ሕይወት አድን ሠራተኞች ደግሞ ለኤኤፍፒ የዜና ወኪል "ከ200 በላይ ሰዎች" ጀልባዋ ላይ ነበሩ ሲሉ ተናግረዋል። ይህ ማለት የጠፉ ሰዎች ቁጥርን ከ60 በላይ ያደርገዋል።

አደጋው ወዳጋጠመበት ካላባሪያ ግዛት የተጓዙት የጣሊያን የአገር ውስጥ ጉዳዮች ሚኒስትር ማቴዎ ፒአንቴዶሲ ቢያንስ እስከ 30 ሰዎች የደረሱበት አልታወቀም ብለዋል።

የጣሊያኑ አንሳ የዜና ወኪል ከሟቾች መካከል የጥቂት ወራት ዕድሜ ያላት ጨቅላ ትገኝበታለች ብሏል።

የጣሊያን የባሕር ዳርቻ ጠባቂዎች 80 ሰዎች በሕይወት መገኘታቸውን ገልጸዋል።

ጀልባዋ ከበርካታ ቀናት በፊት የአፍጋኒስታን፣ የፓኪስታን፣ የሶማሊያ እና የኢራን ዜጎችን አሳፍራ ከቱርክ ስለመነሳቷ ተገልጿል።

በየዓመቱ በብዛት ከአፍሪካ የሆኑ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ስደተኞች ግጭት እና ድህነትን በመሸሽ በጀልባ ጣሊያን ለመድረስ ጥረት ያደርጋሉ።

ጀልባዋ በአስቸጋሪ የአየር ጠባይ ውስጥ እየቀዘፈች ሳለ ከድንጋይ ጋር ከተጋጨች በኋላ ስለመስጠሟ ተገልጿል።

ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የተጋሩ ተንቀሳቃሽ ምስሎች የጀልባዋ ስብርባሪ ከጣሊያን ባሕር ዳርቻ አቅራቢያ ሲንሳፈፉ አሳይቷል።

ከጀልባ መስጠም በኋላ አንድ ግለሰብ ከሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ጋር በተያያዝ በቁጥጥር ሥር ውሏል።

የጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር ጆርጂያ ሜሎኒ በአደጋው የተሰማቸውን ኀዘን ገልጸው፤ ለአደጋው ሕገ-ወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎችን ተጠያቂ አድርገዋል።

ቀኝ ዘመሙ የሜሎኒ አስተዳደር ስደተኞች ወደ ጣሊያን የሚያደርጉትን ጉዞ ከመነሻው በመግታት ወደ የጣሊያ የባሕር ዳርቻዎች እንዳይደርሱ እንደሚያደርግ ቃል ገብቶ ነበር።

አደጋውን ተከትሎ የአውሮፓ ኅብረት ኮሚሽን ፕሬዚዳንት እንዲሁም ፖፕ ፍራንሲስ የተሰማቸውን ኀዘን ገልጸዋል።

የኮሚሽኑ ፕሬዚዳንት ኡርሱላ ቫን ደር ላየን የአውሮፓን የፍልሰት ችግር ለመቅረፍ የአውሮፓ ኅብረት የጥገኝነት አጠያየቅ ሕግጋትን ለማሻሻል ጥረታችንን በእጥፍ መጨምር አለብን ብለዋል።

ፖፕ ፍራንሲስ ደግሞ ሕይወታቸውን ላጡት እና አድራሻቸው የጠፉትን በጸሎቴ አስባቸዋለሁ ብለዋል።

ከእአአ 2014 ጀምሮ አውሮፓ ለመድረስ በሚደረጉ ጥረቶች በሜዲትራንያን ባሕር ከ20 ሺህ በላይ ሰዎች ሕይወታቸው አልፏል አልያም የደረሱበት አይታወቅም።



# ስፖርት



## ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በሳምንቱ መጨረሻ በተለያዩ ውድድሮች ድል ቀንቷቸዋል

ብርሃን ፈይሳ

ባለፈው ሳምንት መጨረሻ በተለያዩ ከተሞች የመም እና የጎዳና ላይ ውድድሮች በስፋት ተከናውነዋል። በእነዚህ ውድድሮችም ላይ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በተሳትፎም ሆነ በአሸናፊነት በስፋት ስማቸውን ማስጠራት ችለዋል። ከእነዚህ ውድድሮች መካከል አንዱ በሃዋሳ የተካሄደው የግማሽ ማራቶን ውድድር ነው። በታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አዘጋጅነት ከሚካሄዱ ዓመታዊ ውድድሮች መካከል አንዱ ይህ ውድድር ሲሆን፣ በወንዶች አትሌት አበባው ደሴ 1:01:52 በሆነ ሰዓት በመግባት የበላይነቱን ሊይዝ ችሏል። ጠንካራ ፉክክር በታየበት በዚህ ውድድር በሁለት ሰከንዶች የዘገየው አትሌት ገመቹ ጊሼ ሁለተኛ ሲሆን፤ አንድ ሰከንድ የዘገየው ሃፍታሙ አባዲ ደግሞ ሶስተኛ ደረጃን በመያዝ የነሃስ ሜዳሊያውን አጥልቋል። በሴቶች በኩል ደግሞ አትሌት የኔነሽ ደጀኔ 1:12:45 የሆነ ሰዓት አስመዝግባ አሸናፊ ለመሆን ችላለች። በሰከንዶች ልዩነት ተከትለዋት የገቡት አትሌት ብዧገር አደራ እና አጸደ ባዩሳ ደግሞ ሁለተኛና ሶስተኛ ሆነዋል።




በሃዋሳ በተካሄደው ግማሽ ማራቶን ውድድር ቀዳሚ ሆነው ያጠናቀቁ አትሌቶች የ50 ሺ ብር ሽልማት ተበርክቷል፣

በስፔን የተካሄደው የካስቴሎ ማራቶን በወንዶች ኢትዮጵያውያኑ አትሌቶች የበላይነቱን ለመያዝ ችለዋል። ከ5ሺ በላይ ሯጮች የተሳተፉበት ይህ ውድድር፤ ለሩጫ ተስማሚ ከሆኑ ስፍራዎች መካከል አንዱ ሲሆን በዓለም አትሌቲክስ የነሃስ ደረጃ የተሰጠውም ነው። በውድድሩም 2:11:15 በሆነ ሰዓት ርቀቱን የሸፈነው ዳዲ ያሚ ሲሆን፤ ሶስት ሰከንዶችን ዘግይቶ የገባው ለሚ ዱሜቻ ደግሞ ሁለተኛ ደረጃን መያዝ ችሏል። ሌላኛው ኢትዮጵያዊ አትሌት አብርሃም ግርማ ደግሞ አራተኛ ደረጃን ሊይዝ ችሏል።

በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ ደረጃ ባለውና በጃፓኗ ኦሳካ በተካሄደው ማራቶንም በተመሳሳይ ኢትዮጵያውያኑ አትሌቶች ውጤታማ መሆናቸውን አረጋግጠዋል። በወንዶች በኩል አሸናፊ የሆነው አትሌት ኃይለማርያም ኪሮስ ሲሆን ሩጫውን የፈጸመበት 2:06:01 የሆነ ሰዓትም የቦታው ክብረወሰን ሆኖ ተመዝግቧል። በሴቶች በኩልም ፈጣን ሰዓት የተመዘገበ ሲሆን፤ አሸናፊዋ ሄለን በቀለ 2:22:16 በሆነ ሰዓት የቦታው ባለ ክብረወሰን ለመሆን ችላለች። ሌላኛዋ አትሌት በየኑ ደገፋ ደጋሞ ሄለንን ተከትላ በመግባት ሁለተኛ ደረጃን ይዛለች።

በደቡብ አፍሪካዋ ፖርልዛቤት የተካሄደው የ50 ኪሎ ሜትር ሩጫ ሲሆን፤ ኢማኔ ሰይፉ አሸናፊ ሆናለች። ርቀቱ ከማራቶን ውድድር የሚረዝመውና ‹‹አልትራ ማራቶን›› የሚል ስያሜ ያለው ሲሆን በዓለም አትሌቲክስ ዕውቅና የተሰጠው ነው። በዚህ ውድድር በርካታ ሴት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የተሳተፉ ቢሆንም በተለያዩ ኪሎ ሜትሮች አቋርጠው ወጥተዋል። የውድድሩ አሸናፊ መሆን የቻለችው ኢማኔ በበኩሏ የርቀቱን ግማሽ ኪሎ ሜትር 1:30:28 በሆነ ሰዓት መሸፈን ችላለች። ከአጋሮቿ ውጪ ለብቻዋ ስትሮጥ የቆየችው አትሌቷ 40ኛውን ኪሎ ሜትር 2:24:46 በሆነ በሰዓት በማቋረጥ የመጨረሻውን መስመር ለመርገጥ ያደረገችው ጥረት የዓለም ክብረወሰንን ለመስበር በአንድ ደቂቃ ብቻ የዘገየ ሆኖባታል። ይሁንና 3:00:29 የሆነ የቦታውን የምንጊዜም ምርጥ ሰዓት ልታስመዘግብ ችላለች። ከሩጫው በኋላም አትሌቷ ‹‹ስሜቴን ለመግለጽ ቃላቶች የሉኝም፤ በጥቅሉ እጅግ አስደሳች ነው›› ስትል አስተያየቷን ሰጥታለች።

በግማሽ ማራቶንም በርካታ ውድድሮች የተካሄዱ ሲሆን፤ በናፖሊ ታዋቂው አትሌት ሙክታር እድሪስ አሸናፊ ሆኗል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከመም ሩጫዎች ይልቅ በጎዳና ላይ ውድድሮች ላይ እየተስተዋለ የሚገኘው የሁለት ጊዜ የዓለም ቻምፒዮኑ አትሌት ሙክታር ርቀቱን በበላይነት ለመፈጸም የፈጀበት ጊዜ 1:00:27 ነው። በአትላንታ ግማሽ ማራቶን ውድድር ደግሞ አትሌት ጸጋዬ ኪዳኑ 1:00:39 በሆነ ሰዓት በመሮጥ አሸንፏል። በዚህ ውድድር የሴቶች ምድብ ላይም ሰላም ፈንቴ ሶስተኛ ደረጃን መያዝ ችላለች። በሜክስኮ በተካሄደ ሌላ ውድድር ላይም በወንዶች አትሌት ያሲን ሃጂ እንዲሁም በሴቶች ህይወት ገብረኪዳን አሸናፊዎች ሆነዋል።



## ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ
## የግዥ መለያ ቁጥር ግ/ግ/ጨ/2/2015 ዓ.ም

የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ለ2015 በጀት ዓመት water well drilling and construction at AMU referal hospital 2 BH with stainaless steel AMU enterprise farm 1BH and kucha Gogara settlement at Gamo zone ግዥ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

**ሎት 1. Water Well Drilling**

**ስለሆነም በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ የንግድ ድርጅቶች:-**

1. በዘርፉ ህጋዊ እና የታደሰ ኦርጅናል የንግድ ፍቃድ ያላቸው፣ የዕቃና አገልግሎት አቅራቢዎች ሊስት (ዝርዝር) የተመዘገቡና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/ የምስክር ወረቀትና የዘመኑን ግብር ስለመክፈላቸው ኦርጅናልና የድጋፍ ደብዳቤ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ተጫራቾች በኢፌዲሪ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የተመዘገቡበትን /PPA Online/ የምዝገባ ሰርተፍኬት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
3. ስለ ጨረታው የሚገልጽውን የጨረታ ሰነድ ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ግዥና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ጽ/ቤት ወይም አዲስ አበባ በሚገኘው የዩኒቨርስቲው ጉዳይ ማስፈፀሚያ ጽ/ቤት አራት ኪሎ ሮሚና ካፌ ያለበት ህንፃ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 14 ዘወትር በሥራ ሰዓት ለፋይናንስና በጀት አስ/ር/ዳ/ጽ/ቤት ለጨረታ ሰነድ የማይመለስ ብር 300.00 /ሦስት መቶ ብር/ በመግዛት መወዳደር የሚችሉ ሲሆን ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የተቋቋሙበትን የሕጋዊነት ማስረጃ በማሳየት ያለ ክፍያ በነፃ ይሰጣቸዋል፡፡
4. የጨረታ ሰነዱን በታሸገ ኤንቬሎፕ በመጋቢት 7/2015 ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ግዥ አገ/ት ቡድን በተዘጋጀ ሳጥን መክተት ይቻላል፡፡ ጨረታው የሚከፈተው በ4:30 ላይ ይሆናል፡፡ ሰነዱ ታሽጐ ባይቀርብና ተፈላጊ ሰነዶች ቢጐድልበት ኃላፊነቱ የተጫራቹ ይሆናል፡፡
5. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪ ሲፒኦ/ቢድ ቦንድ/

❖ ሎት 1 ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺህ ብር ብቻ/

6. በግዥ መመሪያ አንቀጽ 16.16.4 መሰረት ተገቢውን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ማቅረብ አለባቸው:: የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ከአደራጃቸው አካል የሚሰጥ የገንዘብ መጠን የተገለፀበት የዋስትና ደብዳቤ አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡ በጨረታው በተናጠል የሚወዳደሩ አቅራቢዎች ጨረታ ማስከበሪያ መጠን ከጨረታው ሰነድ በማየት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
7. በከፈታው ቀን ከተጠቀሰው ሰዓት ውጪ ዘግይቶ የቀረበ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም::
8. ግልጽ ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ 90 ቀናት ሲሆን ከተጫራቾች የሚቀርበው ጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና የሚቆየው የመጨረሻ ቀን ለተጨማሪ 28 ቀናት ፀንቶ መቆየት ይኖርበታል፡፡
9. የቴክኒካል ዶክሜንት እና ህጋዊነት ሰነዶችና CPO/bid bond/ ለብቻው ታሽጎ መቅረብ ይኖርበታል:: የቴክኒካል ዶክመንት ኦርጅናልና ፎቶ ኮፒ ለብቻው ታሽጎ መቅረብ ይኖርበታል፡ ፡ ፋይናሻል ኦርጅናል እና ኮፒ ለብቻ በፖስታ ታሽጎ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ማለትም ሰነዱ ላይ ያለውን መስፈርት የሚያሟላ ድርጅት ብቻ ፋይናንሻል የሚከፈት ይሆናል፡፡
10. ለምድቡ ቴክኒካልና ፋይናሻል ለየብቻ በተለያዩ ፖስታ ታሽጎ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ በአንድ ላይ ታሽጎ የቀረበ ፖስታ ተቀባይነት አይኖረውም ወይም ከውድድር ውጪ ይደረጋል፡፡
11. ሁሉም ተወዳዳሪዎች ዩኒቨርሲቲው ባቀረበው የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ ላይ የዋጋ ሰንጠረዥ ሙሉ በሙሉ መሙላት አለባቸው፣
12. ተጫራቾች በቀረበው ዲዛይን መሰረት መወዳደር ይጠበቅባችኋል፡፡
13. ተወዳዳሪዎች በውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ WWDC Grade III እና ከዚያ በላይ የሥራ ፍቃድ ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡
14. ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ውስጥ የተገለፁ ግዴታዎችን ማወቅና መፈፀም ይኖርባችኋል፡፡
15. የጨረታ አሸናፊ ድርጅት ከዩኒቨርሲቲው ጋር ውል በመግባት በውል ጊዜ ውስጥ ሥራውን ሠርቶ የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡
16. ተጫራቾች ማንኛውንም የመንግስት ታክስና የግብር ግዴታቸውንም በሚያቀርቡት የመወዳደሪያ ነጠላ ዋጋ ውስጥ አካተው ማቅረብ አለባቸው::
17. ዩኒቨርሲቲው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::

ለማንኛውም ተጨማሪ ማብራሪያ ከዚህ በታች በተጠቀሱ አድራሻዎች ደውሎ መጠየቅ ይቻላል፡፡
ስልክ ቁጥር +251111577704 /አዲስ አበባ/
ስልክ ቁጥር 0468811415/0468814533 /አርባ ምንጭ

**አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ**